ፍራንዚስካ ዋሻ & ቶም ሴሜልሮት

# ሰላም አዲስ አበባ

## የአንበሳው ሌዎን አስገራሚ ጉዞ በአዲስ አበባ



Behindertenverband Leipzig e.V.

**Imprint**

1. Edition, 2022, 4.000 Pieces
Publisher:
Behindertenverband Leipzig e.V.
Bernhard-Göring-Straße 152, D-04277 Leipzig
Tel.: 0341 / 30 65 120
E-Mail: kontakt@behindertenverband-leipzig.de
Website: www.behindertenverband-leipzig.de

Text: Franziska Höhle
Illustration: Tom Semmelroth, Franziska Höhle & Kinder
Proof-reading: Celeste Meisel. André Winkler
Printing: DRUCKHAUS DRESDEN part of RCOMGRUPPE
ISBN: 978-3-9817412-2-3

Reproduction, including excerpts, only with
permission and indication of source.

**Donation accounts of the Disabled Association Leipzig e.V.:**
Sparkasse Leipzig
BIC: WELADE8LXXX
IBAN: DE04860555921111105940

Hypo Vereinsbank
BIC: HYVEDEMM495
IBAN: DE36860200860008409269

**Funded by**

Gefördert durch die Aktion Mensch

Stadt Leipzig
Sozialamt

Leipzig Stiftung
Bürgerschaftliche Tradition seit 1799

Salus BKK
Mit gutem Gefühl krankenversichert

BARMER

The book is funded by BARMER as part of the self-help promotion according to § 20 h Social Code Book V: Warranty claims from the health insurance company cannot arise from this. The Behindertenverband Leipzig e. V. is fully responsible for content and design.

**With support of**

Sächsische Landeszentrale für politische Bildung

በታዳጊዎች በተሰሩት የተለያዩ ምናባዊ
ስዕላትና በአጠቃላይ ስለነበረን ድንቅ
ጊዜ አናሌና፣ ቻርሎቴ፣ ኤዳ፣ ጃኔ፣





ሊያ፣

ሊሊ፣

ሚሌና፣

ሳራ

እና

ሳራ

እና ቪሊ

ልናመሰግናችሁ

እንወዳለን።

ፍራንዚስካ ዋሻ

# ሰላም አዲስ አበባ !

## የአንበሳው ሌዎን አስገራሚ ጉዞ በአዲስ አበባ



# ማውጫ


መቅድም - **9**

የሳይፐዚግ ጓደኛሞች እራሳቸውን ያስተዋውቃሉ - **11**

ማከዳ እና አስደሳቹ ኢሜይል - **14**

ሰላም ማለት “ሀሎ!” ማለት ነው - **20**

የጫካ መናፍስት ጉዞ - **25**

ማንዳሪን፣ ማርማላታና አንድ ለየት ያለ ቁርስ - **35**

ድንቅነሽ - ለኤዲ የምትሆን ጓደኛ - **40**

ቆሎ ይዞ ወደ ታላላቆቹ ፈላሳፎች - **50**

ዘመን የማይሽረው ጓደኝነት - **55**

የማይረሳ ግንኙነት - **61**

ኤዲ! ተነሳ - **64**

የተከፋው አው - **71**

ሁለት ልቦችና አንድ አዲስ ሐገር - **80**

ትርጓሜ - **82**

የብሬል ፊደሎች - **85**

የጣት ምልክቶች - **87**

ስዕሎች (ፒክቶግራም) - **88**

የሎርም ፊደላት - **90**

ምስጋና - **91**



# መቅድም

የኢትዮጵያ ዋና ከተማ በሆነችው አዲስ አበባና በላይፕዚግ መካከል
ለረጅም ዘመናት የቆየ ጥብቅ ግንኙነት የነበረ ሲሆን ይህ ግንኙነትም
በ 2004 ዓ.ም በከተሞቹ መሀል በተፈጠረ የወዳጅነት ውል ከፍ
ወዳለ ደረጃ ለማደግ ችሏል። በዚህም የተነሳ ሁለቱም ከተሞች የአካል
ጉዳተኛ ሰዎችን ሕይወት የተሻለ ለማድረግ “አካታች ማሕበረሰብ”
በመባል የሚታወቀውን የጋራ ፕሮጀክት አንድ ላይ በመተባበር
ለማከናወን ችለዋል። በሁለቱም ቦታዎች ላይ ጉብኝት ማድረግ
የተቻለ ከመሆኑም በላይ የልምድ ልውውጥም ለማድረግ ተችሏል:
: አዲስ አበባ በርካታ ኪሎ ሜትር ርዝመት ያለው የአይነስውራን
መርጃ ሲስተም ያለው መንገድ ያላት ቢሆንም፤ ሆኖም ግን ልክ
እንደ ላይፕዚግ ከተማ በርካታ ችግሮች ያሉበት ነው። ላይፕዚግ
ውስጥ ብስክሌቶች ወይም ማስታወቂያ መንገድ ላይ የሚያስቀምጡ
ሰዎች እንቅፋት እንደሚፈጥሩት ሁላ አዲስ አበባ ውስጥም ሞተር
ሳይክሎች እንቅፋት የሚፈጥሩ መሆናቸውን ልንገነዘብ ችለናል።
ከዚህም በተጨማሪም መንገዶቹ በራሳቸው ሲሰሩ በትክክል የተሰሩ
አይደሉም። በሁለቱም በኩል ያለጥርጥር ግልጽ የሆነው ጉዳይ፤
የሁለቱም ከተሞች ማሕበረሰቦች የተለያየ መሰረታዊ የሆነ የባህል
ማንነት ልዩነት ያላቸው ቢሆንም፤ አንዳንድ ጊዜ ችግሩን እንደ ችግር
የመቀበልና የአካል ጉዳተኞች ያለችግር የሚንቀሳቀሱበትን ሁኔታ
የማወቅ እንዲሁም የማክበር ውስኑነት በሁለቱም ላይ ይታያል።
ስለሆነም በግንባታ ስህተት የተፈጠሩ ችግሮችን ማስወገድ እንዲሁም
በጭንቅላታችን ውስጥ ያሉ የችግሩ መሰናክሎችን መቅረፍ ያሻል።
በሰዎች ጭንቅላት ውስጥ ያለው ችግርን ማሕበረሰቡን ስለጉዳዩ ግንዛቤ
እንዲያገኙ በማነቃቃትና በማስተማር ሊወገድ ይችላል። ሁለቱም
ወገኖች ይህንን ዓላማ በመከተል በተለይም ልጆች ላይ መስራት መቻል
መጀመር ይኖርባቸዋል። ከዚህ መሰረታዊ ሐሳብ እሳቤ በመነሳትም
ከአሁን ጀምሮ ይሕ መጽሐፍ በሶስት ቋንቋዎች እንዲዘጋጅ ይደረጋል:
: ይህንን ጉዳይ ልጆች በሕብረት እንዲተገብሩት ማስቻል፣ የጉዳዩ
ፈጻሚ እንዲሁም አካል እንዲሆኑ ማስቻል በጣም አስፈላጊ ነው።
ለኛ ዋናው ጉዳይ የማሕበረሰቡን የማድረግ ችሎታ በማሳደግ ብቁ
ማሕበረሰብ የሚፈጠርበትን ሁኔታ እንዲኖር ማስቻል ነው። በጉዳዩ ላይ
እያንዳንዱ ሰው የራሱን አስተዋጾ ማድረግ ይችላልም ይጠበቅበታልም:
: የምንፈልገው ይሕንን ጽንሰ ሐሳብ በማሕበረሰቡ ውስጥ እንዲሰርጽ

ማድረግና ተከባብሮ መኖር ማስቻል ነው። በላይፕዚግም ሆነ አዲስ አበባ ውስጥ ይሕንን ጉዳይ ተፈጻሚ ለማድረግ የራሳቸውን አስተዋጾ የሚያደርጉትን ሁሉ ልናመሰግን እንወዳለን። በዚህ ጉዳይ ላይ በተለይ ታዳጊዎችን ልናመሰግን እንወዳለን። ለጉዳዩ ማስፈጸሚያ አክሲዮን ሜንሽን ከሚባለው ፕሮጀክትና ሌሎች በዝርዝሩ ውስጥ ካሉት ተራድኦ ድርጅቶች ድጋፍ ይገኛል። ለነሱም ከልብ የመነጨ ምስጋና እናቀርባለን። ፕሮጀክቱን ለምታስተባብረው ሰራተኛችን ለፍራሲስካ ሆህሌን የከበረ ምስጋና እናቀርባለን፤ ጽሁፎቹን ያዘጋጀችው እርሷ ስትሆን ወደ እንግሊዝኛ የመለሰችውም እሷው ናት። በቁጥር ቀላል የማይባሉ ስዕሎች የተዘጋጁት ከልጆቹ ጋር በመተባበር ነው።

**አካታች ማሕበረሰብ መፍጠር የሚቻለው ሁላችንም ለጉዳዩ ፈቃደኛ ከሆንንና አስፈላጊ የሆኑ ቅድመ ሁኔታዎችን ማሟላት ስንችል ብቻ ነው። ስለሆነም በጋራ እንነሳ።**



Euer / Ihr

Gunter Jähnig
Vorsitzender / Geschäftsführer

im Namen des Behindertenverbandes Leipzig e.V. (BVL)



# የላይፕዚግ ጓደኛሞች እራሳቸውን ያስተዋውቃሉ

## 1



እኔ ሌዎን አንበሳው ነኝ፤ አዎ አንተም በትክክል አይተኸኛል፤ የምንቀሳቀሰው በአካል ጉዳተኞች ተሽከርካሪ ወንበር ነው። ተሽከርካሪ ወንበሩ ለኔ ብዙ ነገሬ ነው፤ ያለሱ አሁን ያለሁትን እኔን መሆን ባልቻልኩ ነበር። ከጓደኞቼ ጋር ለየት ያለ ነገር ማድረግ እወዳለሁ። ቸኮሌት እንዲሁም ከጓደኞቼ ጋር ከምሳ ከሰዓት በኋላ የምንጫወተውን ጨዋታና የበጋውን ጊዜ እወደዋለሁ። በክረምት ለኔ ሁሉም ነገር ትንሽ አስቸጋሪ ነው። በረዶ ወርዶ መሬቱ ላይ ሲከመር በተሽከርካሪ ወንበሬ እንደ ልቤ ከቦታ ቦታ ለመንቀሳቀስ እቸገራለሁ፤ ስለሆነም ብዙ ጊዜ ቤቴ ውስጥ ለመቀመጥ እገደዳለሁ። ይሄ ታዲያ ከጓደኞች ጋር ውጪ እንደመጫወት አያስደስትም። 2

ዋነኛው ጓደኛዬ ብራኢሊ ነው። እሱም አይነስውር ነው፤ ይሄም ማለት ምንም ነገር አያይም ማለት ነው። ጨለማንና ብርሐንን ብቻ ነው የሚለየው። ከተወሰኑ ዓመታት ወዲህ ሞባይል ስልክ አለው፡ ፡ ይህ መሳሪያ እሱን ከሁሉም ሰው ጋር ያገናኘዋል። አንዳንድ ጊዜ እንደ ቀልድ እያደረገ ሞባይል ስልኬ የአይኔ ተለዋጭ ነው ይላል።



ብራኢሊ በእለት ተእለት ህይወቱ ውስጥ ይወቱን ቀለል የሚያደርጉለት የተለያዩ ድጋፍ ሰጪ መሳሪያዎች አሉት፤ ስለሆነም እነኝህን መሳሪያዎች የህይወቴ ረዳት መሳሪያዎች ይላቸውል። ለምሳሌ ጫፉ የሚሄድበትን አቅጣጫ በትክክል እንዲሄድ የሚረዳው የአየነስውራን መንገድ መሪ ረጅም ዱላ አለው። በዚህ ዱላ መሬቱን እየነካካ በየት በኩል መሄድ እንዳለበት ይረዳል። ያለ ሞባይል ስልኩ ብራኢሊንን ማግኘት ወይም ማየት መቼም ቢሆን የሚታሰብ ጉዳይ አይደለም፡ ፡ ሞባይሉን ካልያዘ ኮምፒዩተሩ ላይ ተቀምጧል ማለት ነው። 3

ሌላኛዋ ጥሩዋ ጓደኛዬ ሊዛ ናት። እሷም ጥንቸል ነች። እሷን ለየት የሚያደርጋትደሞ ምንም መስማት አለመቻሏ ነው። ይህም ማለት መስማት የተሳናት ናት ማለት ነው፡ ፡ ደንቆሮ ናት ብሎም ማለት ይቻላል። ሙዚቃ ወይም ምንም አይነት የግንባታ ስራ ትርምስ በሌለበት የጸጥታ ህይወት ውስጥ ነው የምትኖረው። ይህንን ሁኔታ አስበኸዋል? ከሌሎች ጋር መግባባት ትችል ዘንድ መስማት የተሳናቸው ቋንቋ ትጠቀማለች። ይህም ማለት፤ በእጇቿ ምልክት እየሰራች ታወራለች፤ ይህም መስማት የተሳናቸው ቋንቋ ይባላል፡ ፡ ሊዛን የማውቃት ከረጅም ዓመታቶች በፊት ጀምሮ ነው።በዚህም የተነሳ እኔ ራሴ አንዳንዶቹን የምልክት ቋንቋዎች መረዳት ጀምሬያለሁ። እንዲያውም እኔም ራሴ በምልክት ቋንቋ ትንሽ ትንሽ መግባባት እችላለሁ። ግን በጣም ከባድ ነው።4







ቶቢ የሚባለው ጥንቸሉ ጓደኞችን እርስ በእርስ ለመግባባት በብዙ ይረዳናል።እሱ በደንብ መስማት አይችልም። የሚሰማው በጥቂቱ ብቻ ነው፤ በሌ አነጋገር ነገሮችን ጥርት አድርጎ የመስማት ችግር አለበት። ስለሆነም የመስሚያ መሳሪያ ተደርጎለታል፡ ፡ ይህም ለመስሚያ የሚገለገልበት ወይም የሚረዳው መሳሪያ ነው። እሱ መስማት የተሳናቸው ሰዎች ቋንቋ በደንብ ጠንቅቆ ያውቃል። ስለሆነም ከሊዛ ጋር ስንነጋገር በአስተርጓሚነት ይረዳናል። 5



ከዚህ በተጨማሪም ኤሊው ኤዲ አለ፡ ፡ ኤዲ ንቅትቅት ያለና ጨዋታ አዋቂ ነው፡ ፡ ከሱ ጋር ሁል ጊዜ ደስ የሚል ጊዜ ማሳለፍ ይቻላል። እሱን ለየት የሚያደርገው የመማር ችግር ያለበት መሆኑ ነው። ይህም ማለት ብዙ ጊዜ ነገሮችን ቶሎ የመረዳት ችግር አለበት። ስለሆነም ከሱ ጋር ስንነጋገር ቀስ ብለን ለማውራትና ቀለል ያሉ ቃላቶችን ለመጠቀም እንሞክራለን። ይህም “ቀላል የመግባቢያ ቋንቋ” ይባላል። 6

ቦርስተል የሚባለው ጃርትም ጥሩ ጓደኛችን ነው። ሲወለድ ጀምሮ ባለበት ችግር የተነሳ ማውራት ወይም መናገር አይችልም። ስለሆነም ሁል ጊዜ በሱ ቦታ ሆኖ የሚናገርለት ትንሽዬ ኮምፒዩተር ከጎኑ አይለየውም። ይህ ለመነጋገር የሚረዳው መሣሪያ “ቶከር” ይባላል። 7



# ማክዳ እና አስደሳቹ ኢሜይል

በስመ አብ! ዋው ዋው ዋው! መኪናው መንገዱን እየጫረው ሄደ፡ ፡ የተሰባበረው መንገድ በላዩ ላይ ባሉት ጉድጓዶች ውስጥ የሌለው ነገር የለም። መኪኖቹ ሲያልፉ አቧራው ወደላይ ይንሳል። ከመሪው ጀርባ የተቀመጠው ሾፌር የሆነ ነገር ያጉተመትማል። የሚያወራው እኔ በማላውቀው ቋንቋ ስለሆነ ምን እያለ እንደሆነ ሲገባኝ አልቻለም፡ ፡ የሆነ ቦታ ደርሰን  ስንታጠፍ ከፊታችን በጣም ብዙ የፍየል መንጋ መንገዳችንን ዘግቶብን ሳይ ለአጭር ጊዜ ደንግጬ ነበር። ሾፌሩ ፍየሎቹን ለማባረር ጥሩንባውን ነፋው። በዚህ ጊዜ መኪናው በድንገት ተንገጫግጮ ቀጥ ብሎ ቆመ። በመስኮት በኩል አሻግሬ የሚሆነውን ሁሉ እመለከት ስመለከት ከፍየሎቹ ትርምስ እንዲሁም ከደረቀውና አሸዋማው መሬት ላይ ትልቅ የአቧራ ዳመና ሲነሳ ይታይ ነበር። 8

የት ነው ያለነው? አሁን ምን ማድረግ ነው ያለብን? ልቤ በድንጋጤ ትዘላለች፤ በሌላ በኩል ሙቀቱም ከአቅሜ በላይ እየሆነብኝ እንደመጣ እየታወቀኝ ነው። በሐይል ጠምቶኛል፤ አፌም በጣም ድርቅ ብሏል፡ ፡በድንገት የሆነ እጅ ትከሻዬን ሲነካኝ ተሰማኝ። ማክዳ ናት “አትፍሪ፤ ሹፌሩ አቢ ፍየሎቹ መንገዱን ሰለዘጉበት መኪናውን ማቆም ስለነበረበት ነው። ፍየሎቹ በየእለቱ ከአንዱ የግጦሽ ቦታ ወደ ሌላኛው የግጦሽ ቦታ እየተዘዋወሩ ነው የሚስማማቸውን ሳር የሚያገኙት። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ አልፈው ሲያልቁ ጉዟዋችንን እንቀጥላለን” ብላ አረጋጋችኝ። እኔም የማክዳን ደግ ፊት ዞር ብዬ አየሁት። ሳቋ ፍጹም ከውስጧ የሆነና በቀላሉ የሚጋባ አይነት ነው። ወዲያውኑ በድንገት ውስጤ ሲረጋጋ ተሰማኝ። ከዛም አብረን ሆነን እረኞቹ ፍየሎቹን በአንድ ላይ አድርገውና መስመር አስይዘው ለመንዳት ሲሯሯጡ ማየት ጀመርን።በፍጹም ቀላል የሚባል ስራ አይደለም።

አሓ፤ ይሄ ሁሉ ምንድን ነው? ብለህ ትጠይቅ ይሆናል፡
፡ ማክዳ ማን ናት? የመኪናው ሾፌር የሚናገረው
ቋንቋ ምንድን ነው? ወዴት ነው የሚሄዱት?



ከመጀመሪያው ብጀምር ሳይሻል አይቀርም። በግምት ከአራት ሳምንታት በፊት በቆንጆዋ የመኖሪያ ከተማዬ ላይፕዚግ ውስጥ ነበርኩ። በአንድ ከበድ ባለ የክረምት ቀን የጸሐይዋ ብርሐን በመጋረጃዎቹ መሐል ባለው ቀጭን ክፍተት ውስጥ ወደ ቤት ውስጥ በምትገባው የጸሀይ ብርሐን ከእንቅልፌ ነቃሁ። የጸሐይዋ ብርሐን ፊቴ ላይ ያለውን የጺሜን ጸጉር ለሰሰ ባለ ሙቀት እየዳሰሰ ፊቴ ላይ ደስ የሚል ሙቀት ፈጥሮልኛል፡ ፡ ሁኔታው ሁሉ የጸደይ ወቅትን ነበር የሚመስለው። ይሄ ግን ሲሆን የሚችል ነገር አልነበረም። ወሩ ታሕሳስ ሲሆን ውጪ ያለው ቅዝቃዜም በጣም ሐይለኛ ነበር።ለእንደኔ ያለው አንበሳ ግን ይሄ ምንም ማለት አይደለም። እኔ ጸሐይ፣ ሙቀትና የበጋን አየር በጣም ነው የምወደው።




በመኖሪያ ከተማዬ ላይፕዚግ ውስጥ በርካታ ድንቅ የሆኑ የበጋ ጊዜያቶችን አሳልፌያለሁ። ለምሳሌ ያህልም ከጓደኞቼ ብራኢሊ፣ ኤዲ፣ ቦርስቴል፣ ሊዛ እና ቶቢ ጋር የላይፕዚግን መካነ አራዊት ጎብኝተናል። በተጨማሪም ሊሸተናው በሚገኘውና የጸሐይ ፓርክ በሚባለው ውስጥ በሚገኘው ለአካል ጉዳተኞች ተብሎ በተሰራው ትልቁ የሚሽከረከር መጫወቻ አብረን ተጫውተናል። ለአካል ጉዳተኞች ተብሎ የተሰራ ማለት ማንኛውም ሰው ያለ ምንም ችግር ሊወጣጣበት የሚችል ሆኖ የተሰራ ማለት ነው። ለምሳሌ አንድ ቤት ደረጃ ብቻ ሳይሆን ሊፍት ወይም ወደ ላይ ለመውጣት የሚያገለግል ልሙጥ ደረጃ ነገር ካለው ይሄ ለአካል ጉዳተኞች ተብሎ የተሰራ መወጣጫ ያለው ቤት ነው ማለት ይቻላል። እኔም በተሽከርካሪ ወንበሬ ሆኜ ያለምንም ችግር ወደ ሕንጻው መውጣትና መውረድ እችላለሁ ማለት ነው።

አየህ የተለያዩ ቆንጆ ነገሮችን በጋራ ሆነን እናደርጋለን ማለት ነው። ሆኖም ግን ሁሉም ነገር ለኛ ለአካል ጉዳተኞች ቀላል ነው ወይም አልጋ በአልጋ ነው ማለት አይደለም። እያንዳንዳችን ለየት ያለ ነገር አለንና።

በጣም ደስ ያለኝ ግን ከጥቂት ጊዜ በፊት ከጓደኛዬ ማከዳ አንድ አስደሳች ኢሜይል የደረሰኝ ጊዜ ነው በጣም ነበር የተደሰትኩት፡ ፡ ማከዳ አዲስ አበባ የምትኖር አንበሳ ሴት ናት። ይህንን ሰምተህ ታውቃለህ? አዲስ አበባ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ ናት። በምስራቅ አፍሪካ የምትገኝ፤ ከዚህ በጣም ሩቅ ቦታ ላይ ያለች ሐገር ናት። አዲስ አበባ በጣም ብዙ ነዋሪ ያለባት በጣም ትልቅ ከተማ ናት። ከጥቂት አመታት በፊት ላይፕዚግ ውስጥ በአንድ የተለያዩ ሰዎችን የማገናኛ “በከተማ ውስጥ ከተማ” የተሰኘ ፕሮጀክት ላይ ነው የተዋወቅነው፡ ፡ ሁሉም ሰዎች አንድ ላይ ሆነው አንድ ሳምንት ሙሉ የሚፈልጉትንና ሊሆን ይገባዋል ብለው በግላቸው የሚያስቡትን አይነት ከተማ በጋራ ይገነቡ ነበር። ማንኛውም ሰው መሳተፍ ይችል ነበር። ትንሽ ሆነ ትልቅ፣ የአካል ጉዳት ያለበት ወይም የሌለበት፣ ከየትም ሀገር የመጣ ቢሆን ችግር የለውም። ላይፕዚግ ከአዲስ አበባ ከተማ ጋር ለየት ያለ ግንኙነት አላት፤ ሁለቱ ከተሞች እህትማማች ከተሞች ናቸው።  ስለሆነም ነው የኢትዮጵያ ተወካዮች በጨዋታው ላይ

ላይፕዚግ ሊገኙ የቻሉት። ማከዳን የተዋወቅኋት በአንድ ጸሀያማ በሆነ ቀን ነበር። እሷ ምንም አይነት የአካል ጉዳት የለባትም፤ ጥልፍ ስትጠልፍ ደሞ በጣም ጎበዝ ናት።  ሎሚ እየጠጣን በአንድ ጨርቅ ላይ አንድ የኢትዮጵያ አንበሳ ጠለፈችልኝ፤ እኔንም አንበሳ እንዴት መጥለፍ እንደሚቻል አስተማረችኝ። አንበሳ የሁለቱም ከተሞች አርማ ነው - የላይፕዚግና አዲስ አበባ። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ጓደኛሞች ሆንን። ከዛም ማከዳ ወደ ኢትዮጵያ ከተመለሰች በኋላ አዲስ አበባና ላይፕዚግ ውስጥ ስለምናሳልፈው ህይወት በኢሜይል እንጻጻፋለን። በደብዳቤ መጻጻፉ በጣም ጊዜ ይፈጃል፡ [9]



ውድ ሌዎን!
ደህና እነደሆንክ፣ ጤንነትህ የተጠበቀ እንደሆነና ጠንካራ እንደሆንክ ተስፋ አደርጋለሁ። እኔ ደህና ነኝ። ኢትዮጵያ ወስጥ የዝናቡ ወቅት ገና ማለፋ ነው፤ ስለሆነም ሐገሩ ሁሉ ማበብ ጀምሯል። በየቀኑ ወደ ዩኒቨርሲቲ እሄዳለሁ። ዩኒቨርሲቲ ማለት አንድ ለየት ያለ ትምሕርት ቤት ማለት ነው። አንድ ሰው መደበኛውን ትምህርት ቤት ካጠናቀቀ በኋላ በቀጣይ የበለጠ ለመማር ነው ወደዚያ የሚኬደው። እኔ ትምህርቴን ጠንክሬ ነው የምማረው፤ ጓደኞቼንም እዛ ስለማገኛቸው በጣም ደስተኛ ነኝ። ከጥቂት ቀናት በፊት አንድ ጓደኛዬ አገኘኝና ስለታናሽ ወንድሙ አጫወተኝ፤ ስሙም ካሸን ይባላል። ካሸን ገና ሕጻን እያለ የሆነ በሽታ ይዞት ነበር፤ ስለሆነም ካዛን ጊዜ ጀምሮ መሄድ አይችልም።   ስለሆነም እናቱ ሁል ጊዜ አዝላው ነው የሚንቀሳቀሰው።  አሁን ካሸን አድጓል ስለሆነም ክብደቱ ጨምሯል። በዚህም የተነሳ እደ ውጪ መውጣት ትቶ እቤት ውስጥ ቁጭ ብሎ ነው የሚውለው። ከጓደኞቹ ጋር መገናኘት አቁሟል። ስለሆነም በጣም ያዝናል። ከዚህም በተጨማሪ በቅርቡ ትምህርት መጀመር አለበት። ተንቀሳቃሽ ወንበር ያስፈልገዋል! ሆኖም ግን እዚህ እኛ ሀገር ኢትዮጵያ ውስጥ እንደዚህ አይነት ነገር ማግኘት በጣም አስቸጋሪ ነው፤ ቤተሰቦቹም ምን ማድረግ እንዳለባቸው ግራ ገብቷቸዋል። ከዛ እኔ ስላንተ አሰብኩ! የኤሌክትሪክ መንቀሳቀሻ ወንበር ከማግኘትህ በፊት የሚገፋ ተንቀሳቃሽ ወንበር ነበረህ አይደል? ይሄንን ካሸን ቢያገኝ በጣም አሪፍ ነበር። እኔን አዲስ አበባ መጥተህ ብትጎበኘኝ ምን ይመስልሀል? አዲስ አበባ የአማርኛ ቃል ነው፤ ትርጉሙም “አዲስ የሆነ አበባ” ማለት ነው። በጣም ድንቅ ከተማ ናት፤ ከተማዬን ባስጎበኝህ በጣም ደስ ይለኛል። በአጋጣሚውም ለጨጨዋው ካሸን ተንቀሳቃሹን ወንበር ይዘህለት ልትመጣ ትችላለህ አይደል? ደውልልኝና ሐሳቡን እንዴት እንዳገኘህው ንገረኝ።
ከብዙ ሰላምታ ጋር፤ ያንተው ማክዳ



አሁን በጣም ይገርመኛል። ግልጽ ነው፤ አለምን ማየት ደስ ይለኛል: : ሆኖም ግን እንደዚህ በጣም ሩቅ ቦታ የሚገኝ ሐገር! እስከዛ ሰዓት ድረስ ስለ እንድዚህ አይነት ነገር አስቤ አላውቅም ነበር: : እንዴት አስጨናቂ ነው። ትክክለኛ የጀብደኛ ጉዞ። ከምንም በላይ ደሞ ጨጨዋውን ካሸንን መርዳት እፈልጋለሁ። ማክዳ እውነቷን ነው፤ በእውነትም የኤሌክትሪክ ተንቀሳቃሽ ወንበሩን ካገኘሁ ጊዜ ጀምሮ የሚገፋው ተንቀሳቃሽ ወንበር ለኔ አያስፈልገኝም። ታዲያ እንዲህ ከሆነ አንድን ሌላ ሰው ለምን አላስደስትበትም። አዎ! ይህ የግድ መሆን ያለበት ነገር ነው። ወደ አዲስ አበባ እሄዳለሁ: : ሆኖም ግን ብቻዬን አይደለም - ጓደኞቼን ይዤ ነው የምሄደው!

# ሰላም ማለት “ሀሎ!” ማለት ነው

አአአአአሕሕሕሕ! ሌዎን፤ ይህንን ተመልከት! እያለ ኤዲ ትከሻዬን ሲነቀንቀኝ እኔ ገና ወደ ራሴ አልተመለስኩም ነበር። በአውሮፕላን የተወሰኑ ሰዓታት ከበረርን በኋላ ጠዋት ሲነጋጋ ላይ አዲስ አበባ ደረስን። ኤዲና ብራኢሊ በበረራ ላይ እያሉ የኢትዮጵያ ሕጋዊ የስራ ቋንቋ የሆነውን የአማርኛ ቋንቋን እየተንተባተቡ በደስታ የመጀመሪያዎቹን ቃላቶች እየተለማመዱ ነበር። እኔ ግን አይኔን እንኳን ለመግለጽ በጣም ተቸግሬ ነበር። በተንቀሳቃሽ ወንበር ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ በጣም ጥሩ ነው ሆኖም ግን ብዙ ጊዜ በጣም አስቸጋሪ ነው። ስለሆነም በጉዞ ወቅት ብዙውን ሰዓት በመተኛት ነው የማሳልፈው። አሁን ግን  በጣም ንቅት ብያለሁ። የአውሮፕላኑ አስተናጋጆችና የአውሮፕላን ማረፊያው ሰራተኞች ረድተውኝ ተንቀሳቃሽ ወንበሬን አግኝቼዋለሁ። ተሳፋሪዎቹ ሁሉ በአውሮፕላኑ መንደርደሪያ ሜዳ በኩል አልፈው ወደ አንድ አውቶቡስ ይሄዳሉ፡ ፡ ከዛም አውቶቡሱ ወደ አውሮፕላን ማረፊያው ህንጻ ያደርሳቸዋል።







ያውና! እየወጣች ካለችው ጸሐይ ፊት ለፊት የእንጦጦ ተራራ በኩራት ጉብ ብሏል። የጸሀይዋ ብሩህ ብርሀን ወርቃማ ቀለም ያለው እንዲያበራ አድርጎታል።

እንጦጦ፤ ከተማዋን ወደ ታች የሚመለከታት የሰንሰለታማ ተራሮች ጫፍ። ብራኢሊ ጸሀይዋ በታራራው አናት ላይ ስትወጣ ለማየት ባለመቻሉ ትንሽ እንደ ማዘን ብሏል። እኔና ኤዲም በተቻለን መጠን ያለውን ሁኔታ በሰዕላዊ መልኩ ልናብራራለት እንሞክራለን። ዋው! እንጦጦ! በጣም ድንቅ አይደለም? ጫፉ ላይ የባህር ዛፍ ደን ብቻ አይደለም ያለው፤ ከብዙ አመታት በፊት ንጉስ ሚኒሊክ  ሁለተኛ ከባለቤታቸው ጋር ተራራው ላይ ይኖሩበት ነበር፤ አዲስ አበባንም የቆረቆሯት እነሱ ናቸው፤ ስሟንም „አዲስ አበባ“ ብለው የሰየሟት እነሱ ናቸው።

ወደ ኋላዬ ዞር ስል የማክዳን አይኖች በሐይለኛው ተከፍተው አየኋቸው። ሳቅ እያለች አንገቴ ላይ ተጠመጠመችብኝ። በዚህ ደረጃ በሓይለኛው እንደናፈቀችኝ ልብ አላልኩም ነበር። „እህስ„ የታሉ ታዲያ ሌሎቹ? ሲዛና ቶቢ? ቦርስትልም የለም! ገና አውሮፕላን ውስጥ ናቸው ነው? እያለች በመፈለገ አይነት ሁኔታ የአውሮፕላን ማረፊያውን መንደርደሪያ ዙሪያ ገባውን አማተረች። „እምም፤ አይ እንደዛ አይደለም„ ሌሎቹ ለመምጣት አልቻሉም ብዬ መለስኩላት። ሲዛ ሂፕ ሆፕ ትደንሳለች። እናም ሰሞኑን ሙኒክ ከተማ ከሚገኘውና አባላቱ በሙሉ መስማት የተሳናቸው ከሆኑት ኮሪዮ ኮንስ ከሚባለው የዳንስ ቡድን ጋር የዳንስ ውድድር አለባት። ቶቢ ደሞ እሷን አጅቦ ሄዷል። ሲዛ በጣም ስለተጨነቀች ቦርስቴልም ጠንከር እንድትል በማለት አብሯት ሄዷል። የኛ መሪ ቃል እኳ ዝም ብሎ አይደለም „እያንዳንዱ ለሁሉም፤ ሁሉም ለእያንዳንዱ„ የተባለው። „አጎ„ ማክዳ በመስማማት አንገቷን ነቀነቀች፡ ፡ „ኮሪዮ ኮንስ!„ ሲሰሙት ደስ ይላል። በሚቀጥለው ጊዜ እኔ ወደናንተ ጋር ወደ ጀርመን ሐገር ስመጣ ይሄንን ቡድን የግድ መተዋወቅ አለብኝ፡ ፡ ምናልባትም አንድ ላይ ሆነን እንደንስ ይሆናል! አለችና የቀልድ ሳቅ ሳቀች ማክዳ። በማስከተልም ለሲዛ እንዲቀናት እጸልይላታለሁ አለች፡ ፡ ከዛም እሺ፤ ጓደኞቼ በሉ እንግዲህ እንንቀሳቀስ። ጸሐይዋ እየወጣች ነው፤ ከእኔ ጋር ወደ እንጦጦ እንድንሄድ እጋብዛችኋለሁ አለች። ከዛ በኋላ ሻንጣዎቻችንን ሰብስበን የአውሮፕላን ማረፊያውን ህንጻ ለቀን ወጣን። ውጪ ከወጣን በኋላ ግራ ገብቶን ዝም ብለን መንገድ ላይ ቆምን። ማክዳ ተረጋግታ ትስቃለች። “አትፍሩ፤ መጥተው ይወስዱናል”፡ ፡ እዚህ አዲስ አበባ ሰአት በተለመደወ መልኩ አይደለም የሚቆጥረው፡ ፡ አንዳንድ ጊዜ ትንሽ መጠበቅ ግድ ይላል፤ አንዳንድ ጊዜም ትንሽ ረዘም ላለ ጊዜ መጠበቅ የግድ ይሆናል። እኔም ማክዳ ጋር እስከምንደርስ ብዙ እንቆይ ይሆናል ብዬ ተስፋ አደርኩ። መንገዱ በጣም አደክሞኛል፤ በዛ ላይ ትንሽ እንደ መደናገጥም ብያለሁ። ኤዲ “ሌዎን” እያለ ተጣራ “ምን ሆነህል?” አፍንጫህ አካባቢ ነጭ ሆነሓል። ደሕና አይደለህም? “ድካም ብቻ ነው፤ ትንሽ ደሞ ያዞረኛል” ብዬ መለስኩለት። ያዞረኛል? ከምር? እያለ ኤዲ ተጨንቆ ያየኝ ጀመር። “ምንም ችግር የለውም” “ከአካባቢው ከፍታ” የተነሳ ነው ብሎ ብራኢሲ አቋረጠው። አዲስ አበባ የምትገኘው ከባሕር ጠለል በላይ በ 3000 ሜትር ከፍታ ላይ ነው። በዚህም የተነሳ በከፍታ ቦታ ላይ በመገኘት ከአለም ሶስተኛ ቦታ ላይ ከአፍሪካ ደሞ በአንደኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች። ስለሆነም እንደዚህ አይነት ከፍተኛ ቦታ ያልለመደ ሰው ሊያዞረው ወይም ደሞ የራስ ሕመም ሊሰማው ይችላል። በመሰረቱ እንደዚህ አይነቱ ስሜት



በአጭር ጌዜ ውስጥ ይጠፋል ወይም ይስተካከላል አለ። እኔ ሁል ጊዜ ከልቤ ባጣም የሚገርመኝ ነገር “ብራኢሲ ሁሉንም ነገር ማወቁ ነው”። እንደዛ ከሆነ መጨነቅ የለብኝም ማለት ነው ብዬ አሰብኩ።

ማክዳ በእጇ ወደ አንድ አሮጌ ነጭና ሰማያዊ ቀለም የተቀባ ሚኒ ባስ እያሳየች ”ያውና” ብላ ጮህች። “እዚህ እስካላችሁ ድረስ የምንጓጓዝበት መኪና ይሄ ነው አለች። እሱ ደሞ አቢ ይባላል፡ ፡ ተሽከርካሪ ወንበር ያስፈልገዋል ያልኳችሁ የካሸን ወንድም ነው፤ ሾፌራችንም እሱ ነው። ወደ ፈለግንበት ቦታ ሁሉ ያደርሰናል። በዚህ ጊዜ የሆነ ሰው በሚኒባሱ መስኮት በኩል ብቅ ብሎ “ሰላም ሰላም!” አለ። “ሰላም ማለት ሓሎ ማለት ነው፤ ሄይ ሄይ፤ አቢ እባላለሁ፤ እናም የከተማው ምርጥ ሹፌር ነኝ፤ ሄይ ሄይ” ትንሽ ደንገጥ አልኩ፤ አቢ ግድንግድ የጫካ አሳማ ነው የሚያክለው። ድምጹ ደሞ በጣም ጎርናናና ሓይለኛ ነው። ሳቁ ግን በጣም ደስ የሚልና በቶሎ የሚጋባ አይነት ስለሆነ ሸው ብሎኝ የነበረው ድንጋጤ ከመቅጽበት ጥሎኝ ጠፋ።



ሚኒባሱ ግን ከምር በጣም ነው አሳስቦኝ የነበረው፡፡ መወጣጫ ጣውላ ነገርም ሆነ አሳንሰር (ሊፍት) የለውም፡፡ ማክዳ በተንቀሳቃሽ ወንበር እንደምንቀሳቀስ ረስታው ይሆን እንዴ? አቢ ሻንጣዎቻችንንና ትንሿን ተንቀሳቃሽ ወንበር መኪናው ላይ ጫናቸው፡፡ ከዛም እኔ መጀመሪያ አውቶቡሱን ከዛም ትንሿን ተንቀሳቃሽ ወንበሬን ግራ በመጋባት አይነት ስመለከት አየና፡- “ሄይ ሄይ! አትጨነቅ ጓደኛዬ!፤ እዚህ ኢትዮጵያ ውስጥ እንደ ጀርመን ሐገር ብዙ ጉዳይ የሚያቀሉ መሳሪያዎች የሉም፡፡ ለኛ ታዲያ ችግር የሚባል ነገር የለም፤ ያለው መፍትሄ ብቻ ነው፡፡ ተጠንቀቅ!” አለኝ፡፡ ከዛም ማክዳና አቢ ወደ መኪና ውስጥ እንድገባ ወይም እንድሳፈር ረዱኝ፡፡ አቢ እኔ ልብ ሳልለው ተንቀሳቃሽ ወንበሬን የመኪናው ጣራ ላይ በገመድ አስሮታል፡፡ አቢ ሞተሩን ቀሰቀሰና ጉዟችን ተጀመረ፡፡ ሄይ ሄይ፤ ጓደኛዬ እያደንክ ነው! አለ በትንሿ መስኮት በኩል ወደ ውጪ እያየ፤ እኛ ግን ከግራ ወደ ቀኝ እየተላተምን እየሄድን ነበር፡፡ አቢ ከልቡ እየሳቀና በለሆሳስ እያንጎራጎረ ከመሪው ጀርባ ተቀምጦ ያሽከረክራል፡ ፡ በእርግጥም እየተገረምኩ ነበር፡፡ እንደዚህ የሚጮህና ጠንካራ እንሥሣ አይቼ አላውቅም፡፡ ሰላም አዲስ አበባ - ሐሎ አዲስ አበባ!





# የጫካ መናፍስት ጉዞ



ቀዳዳ፤ ቀዳዳ፤ ቀዳዳ፡፡ የአዲስ አበባ አንዳንድ መንገዶች ከምር ውልቅልቃቸው ወጥቷል፡፡ በጣም አስቸጋሪና ወጣ ገባ ነው፡፡ አዲስ የተሰሩትን ሰማይ ጠቀስ ህንጻዎችና ትናንሽና ጣራቸው እርጅት ያሉ ጎጆዎን እያለፍን ስንሄድ ሚኒባሷ ትዘላለች፡፡ ከራዲዮው ደስ የሚል ጣእመ ዜማ ይንቆረቆራል፤ አቢም አንዴ አብሮ ይዘፍናል ትንሽ ቆይቶ ደሞ ያፏጫል፤ በየመንገዱና ጥጋ ጥጉ ላይ ንግዱ ተጧጡፏል፡፡ ሞተር ሳይክሎች ባለ ጋሪ የመጓጓዣ ዘዴዎችንና ባለ ፈርስ ተንቀሳቃሾችን እያለፏቸው ይሄዳሉ፡፡ ፍየሎች መንገዳችንን እያቋረጡ ያልፋሉ፡፡ የሆነ አሸዋማ ቦታ ላይ ለአጭር ጊዜ ቆም አልን፤ ሽታው በጣም ደስ ይላል፡፡ ብዙ ከመጓጓታችን የተነሳ ለረጅም ሰዓት ምግብ እንዳልበላን አሁን ገና ትዝ አለኝ፡፡ የመጨረሻውን ምግብ ከተመገበን 24 ሰዓት ሊሞላን ምንም አይቀረውም፡፡ በድንገት ሆዴ በሃይለኛው መጮህ ሲጀመር ማክዳ ተገርማ ዞር ብላ ተመለከተችኝ፡፡ “ሌዎን ደህና ነህ? ለምንድነው የምታንኮራፋው? ኤዲ በሳቅ ፈረሰ፤ “አታስቢ ማክዳ ሌዎን እያንኮራፋ አይደለም፤ ትንሽ ሆዱእየጮኸ ነው”፡፡ “እኔ በጣም እርቦኛል” አልኩ“፡፡ ሄይ ሄይ በጣም ተርቤያለሁ? የአንበሳ ረሀብ! እርቦኛል ነው የሚባለው አለ አቢ ከሹፌሩ ወንበር ላይ ሆኖ፡፡ ሁላችንም ተሳሳቅን፡፡ “ሌዎን ትንሽ ብቻ ታገስ”፤ ተራራውን ከወጣንና ሁለት ሶስት መታጠፊያዎችን ካለፍን በኋላ ደረስን ማለት ነው አለች ማክዳ፡፡ እውነቷን ነው፤ ወዲያውኑ አውቶቡሳችን በድንገት በሀይል ተንገጫገጨና ቀጥ ብሎ ቆመ፡፡ ኤዲና ብራኢሊ ከመኪናው ወረዱ፤ ማክዳና አቢ እቃዎቻችንን ከመኪናው ጣራ ላይ እየፈቱ ማውረድ ጀመሩ፡፡ ከዛም ድንገት ሳላስበው እራሴን ተንቀሳቃሽ ወንበሬ ላይ አገኘሁት፡፡ በስተመጨረሻም እንደገና ራሴን ችዬ መንቀሳቀስ በመቻሌ በጣም ደስ አለኝ፡፡ ተጨማሪ እርዳታ የሚያስፈልገኝ መሆኑ ለማንም የሚገርመው ነገር አለመሆኑም በጣም ደስ አሰኝቶኛል፡፡

የማክዳን ግቢ መግቢያ በር አልፈን ስንገባ መጥፎ ስሜት አልተሰማኝም። በድንገት ሁሉም ነገር ልክ እንደ ገነት በጣም አረንጓዴና የተለያየ አበባ ያለበት ሆኖ አገኘሁት። የከተማው ጫጫታ እዚህ የለም። ብራኢሊ ከአቢ ጋር ተጣብቋል።የመሬት መጠቆሚያ ረጅሙን ዱላ በእጁ ቢይዝም፤ መሬቱ ባልተስተካከለ መንገድ ላይ ብዙ ሊረዳው አይችልም። መጀመሪያ ላይ ፈራ ተባ እያለ ነበር የሚንቀሳቀሰው፤ ከዛ ብዙም ሳይቆይ አቢ ጎበዝ ረዳቱ መሆኑን ተረዳ፡ ፡ አቢ ወደ የትኛው አቅጣጫ እንደሚሄዱ በደንብ አርጎ ያስረዳዋል፡ ፡ ከዛም ብራኢሊ መንገዱን መረዳት እንደቻለ ሴረዳ ጹም የመረጋጋት መንፈስ አገኘ። ኤዲ በተቃራኒው ጊዜም ሳይብፈጅበት በየጢሻው እየዘለለ ፍሬ መልቀም ተያያዘ። በአጭር ሰኣትም የማክዳን ግቢ አዳረሰው። የሁሉም ነገር መግቢያ ደረጃ ስሳልነበረው ሁላችንም በቤቱ ውስጥ ወደ የክፍላችን ገባንና እቃችንን አወጣን።







ሄይ ጓደኞቼ! ምግብ ተዘጋጅቷል፤ ሁላችሁም ወደ መናፈሻው ኑ! እያለ አቢ ሲጣራ ሰማሁት። ከዛ ሁላችንም አንድ ላይ በተለያዩ ምግቦች በተሞላው ትልቅ ጠረጴዛ ዙሪያ ተቀመጥን። መሐል ላይ አንድ በጣም ትልቅ ድስት ቀይ ወጥ ይዞ ተቀምጧል። “ህም ያስጎመጃል”፤ ማኮሮኒ በቲማቲም ስጎ ነው የሚሆነው አለ ኤዲ። ማክዳና አቢ ጮክ ብለው ሳቁ። ሄይ ሄይ፤ አይደለም አይደለም! ትንሹ ብረት ለበስ ጓደኛዬ፤ ዛሬ የምንበላው እንጀራ ነው። የኢትዮጵያ ባህላዊ ምግብ ነው ብሎ ብራኢሊ አብራራልን። ማክዳ በእያንዳንዳችን ሳሕን ላይ ሥሥ ዳቦ የመሰለ ነገር እያስቀመጠች ባለችበት ቅጽበት ብራኢሊ አስቀድሞ ሞባይል ስልኩን አውጥቶ ስለ ኢትዮጵያ የባህል ምግቦች በዝርዝር ሊነግረን ተዘጋጅቷል። ኤዲ ”የእንቁላል ኬክ” ይመስላል እያለ በእጆቹ መዳፍ ሳህኑ ላይ ያለውን ምግብ ይነካካዋል። ሄይ ሄይ ኤዲ በጣም አቅም የለውም ቁርጥርጥ ይላል፤ በእጆችህ እኮ በምግብ መጫወት የለብህም! እያለች ማክዳ አጉመተመተች።



አዎ አዎ፣ “ኤዲ እኮ እያደረገ ያለው ትክክል ነው”። ኤዲ በጥርጣሬ አይን እያየኝ ምላሱን ወደ እኔ አቅጣጫ ለማውጣት እየሞከረ ባለበት ሰዓት የአቢ ሐይለኛና ደረቅ ግሳት አቋርጠው። ማክዳ “ብራኢሊ ትክክል ነው” እኛ ሐገር የሚበላው እንጀራ የሚባል ባሕላዊ ምግባችን ትንሽ ቆምጠጥ የሚልና ሥሥ ዳቦ ነው አለች፡ ፡ እንደ ምግብ ማንሻነትም (ሹካና ማንኪያ) ያገለግላል። ይህንን ቶሎ መልመድ ያስፈልጋል። የኢትዮጵያ ማንኛውም አይነት ምግብ የሚበላው በእጅ ነው። ለማባያ የሚሆን ፓስታ፣ ሳልሳ፣ አትክልትና ስጋ ይኖራል። በቀኝ እጅ አነስ ያለ እንጀራ ከቆረጡ በኋላ በእንጀራው ፓስታውን ወይም አትክልቱን ጠቅለል አድረጎ መያዝ ያስፈልጋል፡ ፡ ኤዲ “ሲሰሙት ደስ ይላል” አለና ወደ እንጀራው አመራ። በእጅ ምግብ መብላት - እንደዚህ መብላት መቼ ነበር የሚፈቀደው? አለ።

መጀመሪያ ላይ በእንደዚህ ያለ ሁኔታ መብላት አስቸግሮኝ ነበር፡ ፡ እራሴን እንዳለጨመላልቅና እንዳይሳቀብኝ ብዬ ፈርቼ ነበር፡ ፡ ትንሽ እንደ ማፈር ብዬ ነበር። ማክዳ እንደገና አሳየችኝ። በአፏ ሙሉ አንድ ትልቅ የተጠቀለለ እንጀራ እየጎረሰች “ይሄውልህ” ይሄ እኔ የምወደው ምግብ ነው፤ ወጥ ይባላል፤ አያቴ ናት ያዘጋጀችው አለች። በምትጎርስበት ጊዜ ትንሽ ወጥ ወደ አገጯ ተንጠባጠባት። እኔ ሳቅ ስል፤ እሷ ደሞ በአንድ ትንሽዬ ጨርቅ ብጤ ጠረገችው።ከዛ ማክዳም ሳቀች። ትንሽ አረፍ ካልን በኋላ እንነሳና እንጠጣን እናያለን አለች ማክዳ፡



፡ እኔ ከተማዋን ወደ ታች ለመመልከት መቻሌ ቢያስደስተኝም ትንሽ ፍርሐት ቢጤም ተሰምቶኝ ነበር። ተንቀሳቃሽ ወንበሬ ወደ ተራራው ጫፍ ለመውጣት ያስችለኝ ይሆን? ፈሪ ሆኜ መታየት አልፈልግም። የተንቀሳቃሽ ወንበሬን ቀበቶ በሆዴ ዙሪያ ጥብቅ አድርጌ አስረዋለሁ። ያፈለገ ቢሆን እኔና ጓደኞቼ ይህንን ለየት ያለ የህይወት ተሞክሮ ጀምረነዋል።  ከዚህም በተጨማሪ ጓደኛዬ ብራኢሊ ምንም አይነት ጭንቀት አይታይበትም። እሱ ምንም ነገር አያይም፤ በእርግጠኝነት በምንሄድበት መንገድ ላይም የአየነ ስውራኖች የመንገድ ማወቂያ ወይም መጠቆሚያ መምሪያ አይኖርም። በሱ ቦታ ብሆን ኖሮ የበለጠ እጨናነቅ ነበር። ሆኖም ግን ብራኢሊ የውሀ ኮዳውን በጀርባው በሚያነግተው ቦርሳ ውስጥ አስገብቶ የጸሐይ መነጽሩን አጥልቆ ተዘጋጅቷል። ከአቢ ጋር ስር ስር ማለት ከጀመረበት ወይም አብሮ መሆን ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ደስተኛና የተረጋጋ ሆኗል። ሁለቱ በጣም ጥሩ ጓደኛሞች ሆነዋል።

እኔ በድንገት ትንሽ የሐዘን ስሜት ተሰማኝ። ዋናው ጓደኛዬ ከአቢ ጋር ብቻ ነው ግንኙነቱ፤ አብረው ሆነው ይሳሳቃሉ፣ ይቀልዳሉ፤ ብራኢሊ ከሞባይል ስልኩ ላይ አዳዲስ ነገሮችን ያሳየዋል። አቢ ደሞ በመንገዳችን ላይ ሁሉ እንቅፋት ሊሆኑ በሚችሉ ጉዳዮች ሁሉ ያግዘዋል። ማክዳ አጠገቤ ተቀምጣለች፤ “ሁለቱ እንደዚህ በጥሩ ሁኔታ መግባባታቸው ጥሩ ነው”፤ አይደለም እንዴ? ብላ በጥያቄ አይን ተመለከተችኝ።  “አዎን ትክክል ነው” ሆኖም ግን አቢ ትንሽ ድምጹ ለአቢ የሚጮህበትና ሐይለኛ አይመስልሽም”? እኔ እንጃ፤ ጥሩ ጓደኛሞች የሚሆኑ አይመስለኝም አልኩ።



ማክዳ አይኔን እያየች “አህ ሌዎን” አለችና “በቃ አሁን ኢ ፍትሐዊ አትሁን፤ ሰው እኮ አዲስ ጓደኛ ሲያገኝ ጥሩ ነው” አለች። ከዚህም ሌላ አሁን የሳይፕዚግ ጓደኛሞች ብቻ ሳይሆኑ የአዲስ አበባም ጓደኞች እንዳሉ አትርሳ። ይሄ እኮ በጣም አሪፍ ነገር ነው። እንደሚመስለኝ አንዳንድ ጊዜ አዳዲስ ሰዎችን አልፎ አልፎ ወደ ሕይወታችን ማስገባት ክፋት ያለው አይመስለኝም አለች። እያንዳንዱ ሰው የራሱ ጥንካሬና ድክመት አለበት፤ ስለሆነም አንዱ የሌላውን ድክመት ሲሞላና ሊያግዝ ይችላል። “ሕም በሆነ መልኩ ልክ ነው” ማክዳ እውነት አላት። “ሆኖም ግን እኔና ብራኢሊ ብንረዳዳ መልካም ይሆን ነበር” ብዬ እንደማስብ አምናለሁ አልኳት። ”ይህ ካልሆነ የተገለልኩ አይነት ስሜት ይሰማኛል”። ማክዳም “ይሄ በደንብ ነው የሚገባኝ” አለች፡ ፡ “ሆኖም ግን እኔም አለሁ፤ ሁል ጊዜም እኔ ላንተ አለሁልህ” አለችኝ፡ ፡ ”አንበሳው ልቤ በጣም እየመታ ማክዳ ያለችው ነገር በጣም አስደሰተኝ።” ምናልባትም እኮ አዳዲስ ጓደኞች መተዋወቅ መጥፎ ላይሆን ይችላል። ትንሽ ቆይቶ ጉዟዋችንን ጀመርን። ከዛም ትንሽ በተስተካከለ መንገድ ላይ ከሄድን በኋላ ወደ ወጣ ገባው መንገድ ገባን። ጉዞው ወደ ላይ እየዘለሉና እየነጠሩ መሄድ ነው፤ ማክዳ ግን በጣም ተጠግታኝ ነበር የምትጓዘው። ይህም ለኔ አንድ የሆነ ጥሩ ስሜት ፈጥሮብኛል። “እንጦጦ ንጉስ ሚኒልክ ሁለተኛ በህይወት በነበሩበት ዘመን ብቻ ታሪካዊ የነበረ ቦታ ሳይሆን በቤተ ክርስትያናቱና ገዳማቱ አማካኝነት እንደ አንድ ቅዱስ ተራራ ነው የሚታየው” እያለች ማብራራቷን ጀመረች። “ተመልከቱ ፤ እዚህ ለአዲስ አበባ እንደ ሳምባ ሊቆጠር የሚገባው በጣም ጥቅጥቅ ያለ የባሕር ዛፍ ደን ይገኛል”።

ባሕርዛፍ?! አለ ኤዲ በመደነቅ። “አዎ!ከዚህም በተጨማሪ ባህር ዛፉን ብዙ ሰዎች እንደ ማገዶ እንጨትነት ይጠቀሙታል እያለች ማክዳ ገለጻ አደረገችልን።



ልክ በዚህ ሰዓት ጥቅጥቅ ካለው የዛፎቹ ቅርንጫፎች መካከል የሆኑ ሁለት ነገሮች ወደ እኛ አቅጣጫ ሲመጡ አየን። ሲያዩዋቸው ጭብርር ያሉና ግራ የሚያጋቡ አይነት ናቸው። ደማቅ ቀለም ካለው ጨርቅ ውስጥ የተገመደ ረጅም ጸጉር በየአቅጣጫው ጭብርር ብሎ ይታያል፡ ፡ እኔ ልክ መሬት ላይ እንደተተከለ ሰው ድርቅ ብዬ ተገትሬ ቀረሁ። ብራኢሊም ወዲያውኑ የሆነ የተፈጠረ ነገር እንዳለ ስለገባው አይኖቹን አፍጥጧል። ኤዲ ብቻ ነው ወዲያ ወዲህ እየዘለለ መደበቂያ ቦታ እየፈለገና በቀጫጭኖቹ የባህርዛፉ ዛፎች ጀርባ እራሱን ለመደበቅ እየሞከረ “አዬ አዬ፤ የባህርዛፉ መናፍስት መጡ! ሕይወታችሁን ለማዳን ሩጡ!” እያለ ይጮህ የነበረው። በዚህን ጊዜ ጨፍራራዎቹ ምስሎችም ቀጥ ብለው ቆሙ። አሁን ምንድን ነው የምናደርገው? እነኚህ የጫካ መናፍስት ከኛ ምንድን ነው የሚፈልጉት? ውስጤን በጣም ነው የጨነቀኝ፤ አንበሳው ልቤም እንደ ጉድ እየዘለለ ነው።





አንድ ሐይለኛ ለጆሮ የሚቆረቁር ከባድ ሳቅ በአካባቢው ሰፍኖ ከነበረው ጸጥታ አባነነን። ሐሐሐሐሐ! ሊሆን አይችልም! የባሕር ዛፍ መናፍስት! ሐሐሐሐሐ! እያለ አቢ ከሳቁ ብዛት ኩርምት ብሎ ተቀመጠ። “አልችልም! ሐሐሐሐሐ! ጓደኞቼ፤ እነኚህ እኮ መናፍስት አይደሉም! ማከዳ እንደነገረችን፤ እዚህ ጫካ ውስጥ በጣም ብዙ ለማገዶ የሚሆን እንጨት አለ። ስለሆነም የጫካው መናፍስት እንጨት ለቃሚ እንስቶች ናቸው። በጀርባቸው በጣም ብዙ ለማገዶ የሚሆን እንጨት ተሸክመው ሲያዩዋቸው በጣም ይገርማል። እንጨቱን ገበያ ወስደው ይሸጡታል ወይም ደሞ እቤታቸው በማገዶነት ይጠቀሙበታል። ጣፋጩ እንጀራችን በማገዶ እንጨት ሲጋገር የበለጠ ጣፋጭ ነው። ዮፑህ፤ ፍራቻዬ ጠፋ! ልክ ነው፤ አቢ እውነቱን ነው፤ ልብ ብዬ ስመለከት እኔም አወቅኳቸው። ቀጥ ብሎ የቆመ የደኑ መናፍስት ጸጉር የሚመስለው ነገር የባሕር ዛፉ ቅርንጫፎችና እንጨቶች ናቸው። እንደዚህ በመሳሳቴ አፈርኩ። እንዲያውም አንደኛዋ እንጨት ለቃሚ



ፈገግታ ተላብሳና በፍቅር አይን እያየችኝ ወደ እኔ አቅጣጫ መጣች። ከዛም ከተሸከመችው እንጨት ውስጥ አንድ ቅጠል ያለው ቅርንጫፍ አወጣችና ተሽከርካሪ ወንበሬ ላይ ሰካችልኝ። የባሕር ዛፉ ሽታ በጣም ደስ ይላል። ስለ ቆንጆ ማስጌጫዬ ደስተኛ ሆንኩ፤ ሆኖም ግን ምንም ነገር ከመናገሬ በፊት እንጨት ለቃሚዎቹ ጉዞዋቸውን ወደ ፊት ቀጠሉ።

ወደ ላይ መውጣቱ ቀላል ነገር አልነበረም። መሬቱ ላይ የተጋደሙት የዛፎቹ ሥራ ሥሮችና የወዳደቁት ቅርንጫፎች ለኔ በጣም አስቸጋሪ ነበሩ። ምንም መንቀሳቀስ በሚያቅተኝ ጊዜ ማከዳ ተንቀሳቃሽ ወንበሬን ከስሮቹ ወደ ላይ በማንሳት ትገፋልኝ ነበር። ትንሽ ቆይተን የእንጦጦ ጫፍ ላይ ደረስን።



እይታው በጣም ድንቅ ነው። ከተማዋ በጸሐይዋ ብርሐን ታግዛ ድምቅ ብላለች። ያለንበት ቦታ ከፍተኛ ቦታ ላይ ስለሆነ አየሩ ደስ የሚልና ነፋሻማ ነበር። የባሕር ዛፍ ሽታ አካባቢውን አውዶታል፡ ፡ በድንገት መቼም ቢሆን የሚያንቀላፋ የማይመስለው ከተማ ጾጥ ሲል ይሰማል። ማክዳ እጆቿን ትከሻዬ ላይ ጣል አደረገቻቸውና በፈገግታ ተሞልታ “ይቺ ናት፤ አዲስ አበባ” አለችና አይኖቿን በሩቅ ለማየት አሻግራ ላከቻቸው። ”አዲስ አበባ?” በሚጠይቁ አይኖቹ ዙሪያ ገባውን እያየ። “ለምን አበባ?፤ እኔ አበባ አይታየኝም” አለ ኤዲ፡ ፡ እኔ የሚታየኝ ጫካ ነው፣ እኔ የሚታየኝ አሸዋማና ቀይ መሬት፣ ደስ የሚሉ የጫካ መናፍስቶች ... ወዘተ ናቸው። አበባ ግን አላይም! አለ፡ ፡ በማስከተልም “እሺ እንቀጥል” አለች ማክዳ። እሱን አሳያችኋለሁ አለች። ለማንኛውም አብራችሁኝ ኑ! ሁላችንም ተንቀሳቀስን፡ ፡ ወደ ታች መውረዱ በእርግጠኝነት ቀላል አይሆንም።  ሆኖም ግን ከፊታችን በሚጠብቀን የማይታወቅ ጉዞ ደስተኛ ነኝ።.





# ማንዳሪን፣ ማርማላታና አንድ ለየት ያለ ቁርስ

በሚቀጥለው ቀን ከእንቅልፋችን በጠዋት ነበር የተነሳነው፡ ፡ አየሩ ነፋሻማ ሆኖ ንፋሱ አፍንጫችንን ቀዝቀቅ ያደረገው ነበር። ለቁርሳችን የቀረበልን እንጀራ ነው።
8

ማክዳ ለማባያ የሚሆነን የተለያየ የወጥ አይነትና የተቀቀለ እንቁላል ጠረጴዛው ላይ አቀረበችልን። „ወጡን ስትበሉ ጠንቀቅ እያላችሁ ብላ አስጠነቀቀችን። በተቻለኝ መጠን እንዳያቃጥል አድርጌ ነው የሰራሁት።

በጣም ቀዩ ወጥ ግን በጣም ሊያቃጥል ይችላል። እኛ ቀይ ወጥ እንለዋለን እኔም በጣም ነው የምወደው” አለችን፤ እንኳንም ማክዳ ነገረችን ብዬ አሰብኩ። እኔም የሚያቃጥል ምግብ መብላት ብዙም አልወድም፤ ኤዲንም እስከማውቀው ድረስ ጣፋጭ ነገር ከሚወዱት ኤሊዎች ወገን ነው የሚመደበው፤ የሚያቃጥል ምግብ ብዙም አይስማማውም። ሄይ ሄይ ጓደኞቼ! ሁላችሁም ጥሩ ተኛችሁ? እያለ አቢ ጠየቀ። ዛሬ ረጅሙና ወደ እንጦጦ ተራራ የምናደርገው ጉዞ ከፊታችን ይጠብቀናል። „እኔ አንድ ጥሩ ያልሆነ ደስ የማይል ሕልም አይቻለሁ!“ አለ ኤዲ ከንፈሩን መታ መታ እያደረገ። ከዛም እንጀራውን በእጁ እንደያዘ ወንበሩ ላይ ዘሎ ወጣና ይተርክልን ጀመር፡-

„ሁላችንም እንደገና ወደ እንጦጦ ዳገት ለመውጣት በውድቅት ሌሊት ከእንቅልፋችን ተነሳን።ሌዎን አንድ ትልቅ ተንቀሳቃሽ ወንበር ነበረው። ሁላችንም ወንበሩ ላይ ተሳፍረን ወደ ተራራው ጫፍ እያሽከረከርነው ሄድን። በባሕር ዛፍ የተሞላው ደን ሲያዩት ለየት ያለ ይመስል ነበር። በዙሪያችን የከበቡን ዛፎች ሁሉ እላያቸው ላይ ማንዳሪን አንዥርግገዋል። ሰማዩ ልክ እንደ እንጀሪ ደማቅ ቀይ ሆኖ ማርሜላታ ይመስላል። እኔ ማርሜላቱ እንዴት እንደሚጣፍጥ ለመቅመስ አንደኛው ዛፍ ላይ ተንጠልጥዬ ለመውጣት ስሞክር ተንሸራተትኩና ከብዙ የማንዳሪን ፍሬዎች ጋር በአንድ ትልቅ የወንዝ ዳርቻ ላይ አረፍኩ። የወደቅሁበት





ቦታ አጠገብ አንድ ጀልባ አገኘሁና ተሳፈርኩበት። ጀልባው እሳዩ ላይ ዥዋዥዌ መጫወቻ ፈርሶችና የደን መናፍስቶች ወዳሉበት አንድ ድልድይ ወሰደኝ። እዛ ያሉት ሰዎች ሁሉም ተሰብስበው ማርሜላታ እየበሉ ነበር። በዚህ መሐል በድንገት ከዛፎቹ መሐል የሆነ የሚያበራ ነገር አየሁ። ከዛም ነገርዬው ቀስ በቀስ እየደመቀ እየደመቀ መጣና በድንገት አንድ ትንሽዬ ሴት ጦጣ የምትመስል ነገር ቆማ ያየሁ መሰለኝ። በጣም ቆንጆ ነች፤ አይኖቿ እንደ አልማዝ ያበራሉ፡ ፡ እጇን እያውለበለበች ኤዲ፤ ኤዲዲዲዲድ እያለች ጠራችኝ!



ኤዲ ጠረጴዛው ላይ ቆሞ ባለ በሌለ ሐይሉ ይጮሀል። በዚህ ሰዓት አቢ ብቻ አልነበረም መተንፈስ እስኪያቅተው እየሳቀ ያለው ብራኢሊም ሆዱን ይዞ ይስቅ ነበር። ኤዲ ከዛ “ከጀልባው እንደወረድኩ ወደ እናንተ ልመጣ ፈልጌ ነበር፤ እግሮቼ ላይ የተንጠለጠሉት ማንዳሪኖች ግን የድንጋይ ያህል የሚከብዱ ስለነበሩ መንቀሳቀስ አልቻልኩም በዚህ ሰዓት ነበር በድንገት ከእንቅልፌ የነቃሁት” እያለ አጫወተን።
ኤዲ ተስፋ በቆረጠ ስሜት ውስት ሆኖ ወንበሩ ላይ ቁጭ ብሏል፡
፡ “ላናግራችሁ እፈልጋለሁ” ትንሹ የኤሊ ሰው ግንባሩ ላይ የጭንቀት ምልክት በሚታይበት ሁኔታ ሆኖ ተናገረ። ከዛም ማክዳ ኤዲን ጥብቅ አርጋ እቅፍ እያደረገችው ”አህ ኤዲ፤ አትዘን!” አለችው፡
፡ “አንተንም አኮ አይተሐለች”። እርግጠኛ ነኝ በቅርቡ ደሞ እንደገና ትገናኛላችሁ። “ከዛ ሳቅ እያለች በአይኖቿ ጠቀሰችው። ሆኖም ግን ኤዲ ትከሻውን እየሰበቀ አንድ የእንጀራ ቁራጭ አነሳ። 27 በሚያዳዳው ህልሙ የተነሳ ምግቡን ሙሉ በሙሉ ረስቶት ነበር፡
፡ በሐሳብ ተውጦ ሳይታወቀው በእጁ የያዘውን እንጀራ ጠረጴዛው ላይ ያለው ቀይ ወጥ ውስጥ ነክሮት ነበር። አቢ “ኤዲ ተጠንቀቅ፤ ይሄ በጣም ያቃጥላ...” ብሎ ለመናገር የፈለገውን ሳይጨርስ ኤዲ በእጁ ጠቅልሎ የያዘውን እንጀራ ወደ አፉ ጎረሰው።



አቢ ኤዲን “ብረት ለበሱ ጓደኛዬ! ይሄ ወጥ ነው - የሚያቃጥል ወጥ” እያለ በድንጋጤ ያየው ጀመር። ኤዲ አሁንም ትከሻውን ሰበቀ፤ ሆኖም ግን ብዙም ሳይቆይ ልክ እንደተመታ ቀጥ ብሎ ቀረ፤ ፊቱ ደም መሰለ፤ አይኖቹ በእንባ ተሞሉ።
እንጦጦን በሚያንቀጠቅጥ ድምጽ ጮሆ ያቃጥጥጥጥጥጥላላልልልል ብሎ ጮኸ። ከዛም ማክዳ በአንድ ትልቅ ኩባያ ወተት እስከምታመጣለት ድረስ መናፈሻው ውስጥ ተንከባለለ። “እንካ ጠጣ ይሄንን፤ ለሚያቃጥል ነገር ይሄ ነው መድሐኒቱ!” ብላ ሰጠችው። ኤዲም ወተቱን ጭልጥ አድርጎ ጠጣው። “ውይ፤ ለጥቂት ልሞት ነበር”። በጣም ነው የረዳኝ፤ ማክዳ በጣም አመሰግናለሁ አለና እራሱን አስተካከለ። “ሄይ ሄይ ሄይ”፤ እያለ አቢ ያንን አገር የሚያደባልቀውን ሳቁን ለቀቀውና፤ “ብረት ለበሱ ጓደኛዬ ተጠንቀቅ አለና፡ ወጥ ሁለት ጊዜ ነው የሚያቃጥለው፤ ወደ ሰውነታችን ሲገባና ከሰውነታችን ሲወጣ። ሄይ ሄይ አለ።



# ድንቅነሽ - ለኤዲ የምትሆን ጓደኛ

ከዚህ ሁሉ ደስታ የተሞላበት ቀን በኋላ ትንሽ ከተረጋጋን በኋላ እቃዎቻችንን መልሰን ሰብስበን አሸግን። የአቢን ታናሽ ወንድም ካሸን እና እናቱን ልናገኛቸው ቀጠሮ ነበርን። ሁለቱ የሚኖሩት ከከተማው ትንሽ ወጣ ብለው ሲሆን፤ ማክዳም ወደ ቀጠሮ ቦታችን ለመሄድ እንደተንቀሳቀሱ መረጃው ነበራት። “ሆኖም ግን በስንት ሰዓት እንደሚደርሱ በትክክል መገመት አይቻልም” አለ አቢ። ሂሂሂ የሚመጡት እኮ በአውቶቡስ ነው፤ አውቶቡሱ ደሞ በስንት ሰዓት እንደሚመጣ ማንም በእርግጠኝነት መናገር አይቻልም። ሆኖም ግን ከሰዓት በኋላ በሆነ ሰዓት ላይ እንገናኛለን” አለ አቢ። ስለሆነም ለካሸን ተንቀሳቃሽ ወንበሩን እስከምንሰጠው ድረስ ጊዜ አለን ማለት ነው። ስለሆነም እስከዛ ድረስ አዲስ አበባን የበለጠ ብናያት የተሻለ እንደሆነ ወሰንን። ከዛም ሁላችንም ወደ ነጭና ሰማያዊዋ ሚኒባሳችን ገብተን ታጨቅን፤ አቢም መኪናዋ ዳገቱን እንድትወጣ ያስጨንቃት ጀመር። “አንዱን መታጠፊያ ሲጨርስ ሌላኛው ከዛም ሌላኛውን! እያለፈ አምስት ኪሎ አካባቢ ስንደርስ መኪናውን አቆመ። ከፊት ለፊታችን የኢትዮጵያ ብሄራዊ ሙዚየም ይታያል።

በአንድ ትልቅ በር በኩል አድርገን ወደ ቅጥር ግቢው ውስጥ ገባን፡ ፡ ሁሉም ነገር በጣም በሚያምር መልኩ አረንጓዴ አትክልት ለብሷል፡ ፡ የከተማው ጫጫታ ከኋላችን ቀርቷል። ሙዚየም በጣም እወዳለሁ፡ ፡ ብራኢሊ ስለ ሁሉም ነገር አስቀድሞ በቂ መረጃ ሰብስቦ ነበር፡ ፡ ስለሆነም ገለጻ ያደርግልን ጀመር። “ሙዚየሙ ውስጥ የኢትዮጵያ የባሕል ጥበብ ቅርሶች ይገኛሉ። ለምሳሌ የመካከለኛው የስልጣኔ ዘመን ዕቃዎችን፣ ከአሁን ቀደም የነበሩ ነገስታት ማስታወሻዎችንና ሌሎች በጣም ውድ እንዲሁም ታሪካዊ የሆኑ ነገሮችን ማየት ይቻላል”፡ ፡ “ብራኢሊ የሚለው ሁሉ ትክክል ነው፤ ብላ ማክዳ አቋረጠችውና“ “ሙዚየሙ ውስጥ የሚገኝ ዋናውንና ትልቁን ነገር ግን መርሳት የለብህም አለች። ኢትዮጵያውያኖች ሁሉ በጣም የሚኮሩበትን ነገር”፡ ፡ “ሄይ ሄይ፤ የኛ ሉሲ !” ብሎ አቢ ደረቱን ነፍቶ ተናገረ። ሉሲ ጥንታዊ የሰው ቅሪተ አካል ነች፤ አጽመ አጥንቷ ከመሬት በታች በሚገኘው ክፍል ውስጥ ነው ያለው አለ። በእርግጥም ከብዙ አመታት በፊት






“ስለ ሉሲ ሰምቼ አውቃለሁ” አለ ብራኢሊ። በመቀጠልም “አጽመ እርስቷ ኢትዮጵያ ውስጥ ተቆፍሮ እንደተገኘ አውቃለሁ” አለ፡ ፡ እድሜዋ በግምት 3,2 ሚሊዮን አመት እንደሚገመትና በወቅቱም ቀጥ ብላ መሄድ የምትችል እንደነበረች ይገመታል አለ። ”አቢ በጣም ተደስቶ“ ሄይ ሄይ ሰዎች ትክክል ነው፤ በዚህም የተነሳ የሰው ልጅ ትክክለኛ መገኛው እዚህ ኢትዮጵያ ውስጥ ነው!” አለ። ኤዲ የተገረመ መሆኑ ያስታውቅበታል። “የምን ቅድመ ሰው ነው የምታወሩት?” የኛ ቀደምት የሆነ ሰው እናንተ ጋር ከምድር በታች ከሚገኘው ቤት ውስጥ አለች ነው የምትሉት? ይህቺ ሉሲ የምትሏት ሰውስ ስንት አመቷ ነው? ሶስት ሚሊዮን አመት? ምንም ነገር አይገባኝም አለ። ኤዲ ጭንቅላቱ ውስጥ የሚያስበው ሁሉ እንደ አንድ የጠረጴዛ ቴኒስ ኳስ ከወዲያ ወዲህ እየተላተመ ድብልቅልቅ ስላለበት፤ በፍቅር በሚወደው ሥሥ ወደ ሆነው የብረት ልብሱ ውስጥ ቢደበቅና ነገሮችን በተራ በተራ መልክ ቢያሲዛቸው ደስ ባለው ነበር።



“ብረት ለበሱ ጓደኛዬ፤ አይዞህ” አለው አቢ አጀቹን ትከሻው ላይ ጣል እያደረገበት። በማስከተልም ሁላችንም አብረን ሆነን ሙዚየሙን እንጎበኛለን፤ እኔ ሁሉንም ነገር በእርጋታ አስረዳችኋለሁ” አለው፡ ፡ “እሺ” አለ ኤዲ ከዛም የሆነ ነገር አነሳ፤ “ግን ከምር በእርጋታ መሆን አለበት” አለ። አቢ ሳቅ አለና “እኛ ሐገር ኢትዮጵያ ውስጥ “ኦኬ” ማለት ስንፈልግ “እሺ እሺ” ነው የምንለው አለ። “እሺ እሺ?” ኤዲ ተስማምቶታል። “እሺ እሺ፤ እያለ እየተጣራ ወደ ሙዚየሙ መግቢያ በር እየሮጠ ሄደ። እኛም እየሳቅን ተከተልነው።

መግቢያው በር ላይ ስንደርስ ግን ሁላችንም ቀጥ ብለን ቆመን ቀረን፡ ፡ ኦው አይሆንም! ማናችንም ይህ ይሆናል ብለን አላሰብንም ነበር፡ ፡ ወደ ሕንጻው የውስጥ ክፍል ለመግባት አንድ በጣም ትልቅ የሆነ ደረጃን መውጣት የግድ ነው። ኤዲ ደረጃዎቹን ተራ በተራ እየዘለለ እየወጣ ነበር፤ “አንድ፣ ሁለት፣ ሶስት፣ ... ሰባት፣ ስምንት፣ ዘጠኝ ... አስራ አምስት፣ አስራ ስድስት። አስራ ስድስት ደረጃ ነው! አለ እላይ መግቢያ በሩ ላይ ከደረሰ በኋላ። አስራ ስድስት ደረጃ፤ ኦዬ።



ይሄ እኔ ልወጣው የማልችለው ከባድ እንቅፋት ነው። እንደው እንደምንም ብዬ መውጣቱ ቢሳካልኝ እንኳ፤ ተንቀሳቃሽ ወንበሬ በጣም ከባድ ስለሆነ እሱን ወደ ላይ ማውጣት አይቻልም። ያለ ተንቀሳቃሽ ወንበሬ ደሞ ምንም ማድረግ አልችልም። ስሜታችን ሁሉ በአንድ ጊዜ ቅዝቅዝ አለ። ኤዲ አሁንም ደረጃው ላይ እንደቆመ ነው። “ሊሆን አይችልም፤ እኔ እንደገና እቆጥረዋለሁ“ አለ ከላይ ሆኖ። በማስከተልም እንደገና መቁጠር ጀመረ፤ አንድ፣ ሁለት፣ ...። ማክዳና አቢ የታችኛው ደረጃ ላይ ተቀምጠዋል። ማክዳ በአዘነ አይኗ እያየችኝ፡-“ሌዎን፤ በጣም ነው የማዝነው፤ እኔ ለእናንት የኢትዮጵያን አስደናቂ ታሪክ

ማሳየት እፈልግ ነበር። ሆኖም ግን ሕንጻው ለአካል ጉዳተኞች የሚሆን መግቢያ እንደሌለው ሙሉ በሙሉ ዘንግቼዋለሁ። እኛ ሐገር ኢትዮጵያ ውስጥ ለአካል ጉዳተኞች የሚስማማ መግቢያ የሚለው ነገር አዲስ ነው። እናንተ ሐገር ጀርመን ውስጥ ከሚደረገው በተቃራኒው እዚህ አዲስ አበባ ውስጥ ብዙ ሕንጻዎች ለአካል ጉዳተኞች የሚስማማ መግቢያ ሳይኖራቸው ነው የሚገነቡት፡ ፡ ብዙ ጊዜ የሚገኙት ትንንሽ ደረጃዎች ወይም ደሞ የበሮቹ ስፋት በተንቀሳቃሽ ወንበር ሆኖ ለመግባት የማይሆኑ ጠባቦች ናቸው።“

“ከምር? የሆነ በተንቀሳቃሽ ወንበር የሚንቀሳቀስ ሰው ሲመጣ ታዲያ እንዴት ነው የሚደረገው?” ብሎ ደረጃው መጀመሪያ ላይ ደርሶ የነበረውና ከሌሎቹ አጠገብ እየተቀመጠ የነበረው ኤዲ ጠየቀ፡ ፡ አቢም “ብረት ለበሱ ጓደኛዬ፤ ይሄ በጥም ጥሩ ጥያቄ ነው” በማለት መለሰለት። ኤዲም ይሕንን ጥያቄ ማቅረብ በመቻሉ ተደስቶ ፊቱ ሁሉ በርቶ በኩራት ሳቀ። “እኛ ኢትዮጵያውያን አካል ጉዳተኛ ሆነን ስንኖር እናንተ ሐገር እንዳሉት ለአካል ጉዳተኞች የሚቀርቡትን አይነት ሁኔታዎች እንዲሟሉልን አንጠብቅም። ሆኖም ግን ሌሎች ተስፋ እንድንቆርጥ እንዲያደርጉን ደሞ አንፈቅድላቸውም”። ስለሆነም ሁላችንም እንረዳዳለን። የሆነ ሰው እርዳታ ካስፈለገው፤ የሚያስፈልገውን እርዳታ ወዲያው ያገኛል። ሁላችንም እርስ በእርሳችን እንረዳዳለን። ይህም ማለት ችግር ሲያጋጥመን በጋራ መፍትሄ እንፈልግለታለን። በዚህም የተነሳ የኛ መሪ ቃላችን “ሁሉንም በጋራ” የሚል ነው። “እያንዳንዱ ለሁሉም - ሁሉም ለእያንዳንዱ” ብሎ ብራኢሊ ሲጮህ ኤዲ ወደ ላይ ዘለለ። [33]

ብራኢሊ “እኔ አንድ ሐሳብ አለኝ፤ አንተ ወደ ሙዚየሙ መግባት
የማትችል ከሆነ መዚየሙ ወደ አንተ ይመጣል” አለ፡፡ “ምን እያልክ
ነው?” ብራኢሊ የጸሐይ ሙቀቱ ውስጡ ዘልቆ ሳይገባበት አይቀርም፡
፡ ሙዚየሙ ወደ እኔ ይመጣል? እንዴት ብሎ ነው ሙዚየሙ
መራመድ የሚችለው? አለ ሴዎን፡፡ ብራኢሊ ምን ማለቱ እንደሆነ
ያስረዳ ጀመር፡- “ማክዳ፤ አንቺ ሞባይል ስልክሽን ይዘሸዋል አይደል?
ብሎ ጠየቃት፡፡ ማክዳም ብራኢሊ ምን ለማድረግ እንደፈለገ
ስላልገባት ግራ በተጋባ ሁኔታ ላይ ሆና አንገቷን በአዎንታ ነቀነቀች፡
፡ “በቃ፤ ሁሉም ነገር ቀላል ነው” ሴዎን እና አንቺ እዚህ ውጪው
ጋር አንድ ጥሩ አረንጓዴ የሆነ ቦታ ፈልጉና ቁጭ በሉ፡፡ ኤዲ፣
አቢና እኔ ሙዚየሙ ውስጥ እንገባና ኤግዚብሽኑን እንቀርጻዋለን፡
፡ እናንተም በሞባይል ስልኩ አማካኝነት የጉብኝቱ ተሳታፊዎች
ትሆናላችሁ ማለት ነው” አለ፡፡ አቢም “ሄይ ሄይ ብራኢሊ፤ በእውነትም
አንተ ጀግና ሰው ነህ” አለው፤ እኔም ጥቂት ስለ ብራኢሊ ሐሳብ
ካሰብኩኝ በኋላ አዎ፤ ይሄ ሊሆን የሚችል ነገር ነው አልኩ፡፡





በአንድ ጊዜ ጭልም ብሎ የነበረው የሁላችንም ስሜት ተንኖ ጠፋ፡
፡ የብራኢሊ ሞባይል ስልክ ለኔ እርዳታ ሳገኝበት የሚያስችለኝ
መሳሪያ ይሆናል ብዬ አስቤ አላውቅም፡፡ ከዛም የሙዚየሙን
ጉብኝት በጉጉት እየጠበኩ ከማክዳ ጋር ከሙዚየሙ ፊት
ለፊት የሚገኝ ለማረፍ የሚስማማ ቦታ ፍለጋ ገባን፡፡
አቢ፣ ብራኢሊና ኤዲም ወደ ሙዚየሙ አቅጣጫ ጉዞዋቸውን ቀጠሉ፡፡
ሙዚየሙ ውስጥ በሚገኙትም የኢትዮጵያ ስነ ጥበብ፣ የባሕል የሙዚቃ
መሳሪያዎችና የሐይለስላሴ ዙፋን እየተደነቁ ጉብኝታቸውን ቀጥለዋል፡
፡ በሙዚየሙ ውስጥ በርካታ ታሪካዊ ነገሮች ለእይታ ቀርበዋል፤ ኤዲ
ግን በተለይ ወደ ታችኛው የሕንጻው ክፍል ለመሄድ በጣም ጓጉቷል፡፡
አቢ ያጫወታቸው ታሪክ አሁንም ጭንቅላቱ ውስጥ እየተመላለሰበት
ጥንታዊቷንና ቀደምቷ የሰው ልጅ ቅሪተ አካልን ለማየት በጣም ጓጉቷል፡
፡ ብራኢሊ ከነ አቢ ቀስ ብሎ ተሰውሮ በአይነስውር መንገድ መምሪያ
ዱላው መሬቱን እየዳሰሰ ወደ ታች የሚወስደውን ደረጃ ወርዶ ከመሬት
በፍለጋ ተቆፍሮ ስለወጣው ታሪካዊ ግኝት ወደሚያስረዳው ክፍል ሄደ፡፡
ኤዲ ትግስቱ ተሟጦ አልቋል፡፡ ሁለቱንም አልፏቸው በኢግዚብሽኑ
ውስጥ ወዲያ ወዲህ ይሯሯጥ ጀመር፡፡ አንድ ጊዜ ወደዚያ ይሄድና
ዙሪያውን ዞሮ እንደገና ይመለሳል፡፡ ሆኖም ግን የሚፈልገውን ነገር
ለማግኘት አልቻለም፡፡ ሁሉም ቦታ ያለው የመስታወት ሳጥንና
የተሰቀሉ የሚታዩ ነገሮች ናቸው፡፡ በየመስታወቱ ውስጥ የተለያዩ
ድንጋዮችና ጥቂት አጥንቶች ናቸው ያሉት፡፡ ስለ ታዋቂዋ ቅድመ
ሰው ምንም ሊያገኝ አልቻለም፡፡ ስለሆነም ኤዲ እዝን ብሏል፡፡ ተስፋ
በቆረጠ ስሜት ውስጥ ሆኖ ወደ አቢ ጋር ተመለሰና የታለች ታዲያ?
ተደበቃለች እንዴ? ብሎ ጠየቀው፡፡ሄይ ሄይ ብረት ለበሱ ጓደኛዬ
ማንን ነው እያልክ ያለህው? አለው አቢ፡፡ ኤዲም ተስፋ በቆረጠ
ድምጸት እዝን ብሎ፡- “ይቺ የናንተ ሉሲ ነው ማነው የምትባለው?”



ሲል፤ ሄይ ሄይ ሉሲ! ማለትህ ነው? ና አብረህኝ እንሂድ እዛ ጋር ናት፤ እኔ አሳያችኋለሁ ብሎት ይዟቸው ሄደ፡፡ ሶስቱም አንድ ከመስታወት የተሰራ ቁምሳጥን አጠገብ ሲደርሱ ቆመው መመልከት ጀመሩ፡ ፡ በውስጡ የተወሰኑ የአጥንት ስብስቦች አንድ ላይ ሆነው አጽመ ሰው የሚመስል ሆነው ተቀምጠው ይታያል፡፡ ሄይ “የኛ ሉሲ ማለት ይቺ ነች” አለ አቢ በኩራት መንፈስ ውስጥ ሆኖ፤ ትንሽ ትንሽም የመፈንጠዝ አይነት ስሜት እየተሰማው፡፡ በኤዲ ፊት ላይ ግን ጥያቄያዊ የሆነ ነገር ነበር የሚታየው፡፡ “ይህ የሉሲ ቅሪተ አካል ነው” አለ እያብራራ፡፡ በ 1974 ዓ.ም እዚህ ኢትዮጵያ ውስጥ ነው የተገኘችው፡፡ እናም እስካሁን በአለም ዙሪያ ከተገኙት የሰው ቅሪተ አካላት ይሄኛው በጣም ረጅም ዕድሜ ያለው ነው፡፡ ለዚህም ነው በጣም ታዋቂ የሆነው አለ፡፡ እንደሚገመተው አንድ ሜትር ቁመት



የነበራት እንስት ስትሆን ቀጥ ብላ ቆማም ትሄድ ነበር”፡፡ ምንም እንኳ ኤዲ ትንሽ ያዘነ ቢሆንም የሉሲ ታሪክ ግን በጣም አስደንቆታል፡፡

በተረጋጋ መንፈስ ሆኖ አውደ ራእዩን እየተዘዋወረ እያየና እያንዳንዱን የመስታወት ቁም ሳጥን እየጎበኘ እንዲሁም ከስራቸው የተጻፉትን ማብራሪያዎች እያነበበ ቆየ፡፡ አንድ የሉሲን ምስል የሚያሳይ ስእል ሲያይ አይኖቹ እንደ ብርሀን አበሩ፡፡ አንድ የምታምር ሴት ጦጣ በደረቁ የኢትዮጵያ ተፈጥሮ ላይ ስትንጎማለል የሚያይ መሰለው፡፡ አቢ በድንገት ትከሻውን መታ መታ ሲይስደርገው፤ ጥቂት ደንገጥ እንደማለት አለ፡፡ “ትንሹ ሰውዬ” እንቀጥል አለው፡፡ ዛሬ ማከናወን ያለብን ሌሎችም ጉዳዮች አሉ፡፡ አዎ አዎ አሁን መጣሁ፤ አምስት ደቂቃ ብቻ፤ እባካችሁ! ብሎ ኤዲ ተማጸናቸው፡፡ አቢ መስማማቱን በአንገቱ ንቅናቄ አስውቆት ሄደ፡፡ እሱም መስታወት ውስጥ ያለችዋን ትንሿን ጦጣ በአድናቆት ማየቱን ቀጠለ፡፡ አቢ ከብራኢሊ ጋር ሆኖ ሙዚየሙን ለቅቆ ሲወጣ ኤዲ ብቻውን እዛው ቀረ፡፡



ደስተኛ ሆኖ ወደ ደረጃው እየሮጠ ወጥቶ እንደገና መቁጠር ጀመረ። አንድ፣ ሁለት፣ ሶስት፣ … “ኤዲ!” ኤዲ ቁም፤ የሆነ የሚጣራ ሰው አለ? ሊሆን አይችልም፤ እዚህ ከመሬት በታች ያለ ክፍል ውስጥ ያለው እሱ ብቻ ነው። እንዴ ሊሆን ይችላል። ኤኤኤዲዲዲ! አሁንም እንደገና ተጣራ! የሆነ ሰው ስሙን እየተጣራ ነበር። በደንብ ነበር የሚሰማው፡ ፡ ወደ ኋላ ፊቱን ዞረና ከደረጃው ላይ ዘሎ ወረደ። ከመሰታወት ቁም ሳጥኖቹ ውስጥ አንዱ ተከፍቷል፤ እሷም ቆማለች፤ በክፍሉ መሀል ላይ፡ ፡ አይኖቿ ያበራሉ፤ ፈገግታዋ ምትሐታዊ ነው። ኤዲ “አንቺ ነሽ?”፤ በሕልሜ የምትታይኝ ትንሿ ጦጣ” እያለ ተጣራ ። “ሰዎች እኔን ሉሲ ይሉኛል” አለችው ትንሿ ጦጢት። ስሜ ግን ድንቅነሽ ነው፤ ይሄም የአማርኛ ቋንቋ ሲሆን ትርጉሙም አንቺ ድንቅ የሆንሽ ማለት ነው። “ድንቅነሽ” ሲሰሙት ደስ ይላል” ብሎ መለሰ ኤዲ፡ ፡ ጓደኞቼ ውጪ እየጠበቁኝ ነው። አብረሽኝ ሄደሽ ልትተዋወቂያቸው አትፈልጊም አላት። “እሺ እሺ”፤ ብላ መለሰችለትና አንድ ላይ ሆነው ደረጃውን መውጣት ጀመሩ።

ኤዲ ሲያያይት ደረጃውን ስትወጣ በደስታ ወዲያና ወዲህ የምትዘል መሰለው። “ሄይ ድንቅነሽ እግርሽን ምን ሆነሽ ነው? ስትራመጂ ትንሽ ለየት ያለ አረማመደ ነው ያለሽ ብሎ ጠየቃት። እሷም በድንገት ዞር ብላ እያየችው፡-“ሲያዩኝ የማስቅ አይነት እመስላለሁ?” አልችና ታሪኩን አጫወተችው። በጣም ከረጅም ጊዜ በፊት ከአንድ የዱር አራዊት ጋር ተጋጭተን አደጋ አጋጥሞኝ ነበር፤ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እያነከስኩ ነው የምራመደና በትክክል መራመድ አልችልም አለችው። ኤዲን እዝን ባለ አይን እያየችው እንባዋ ቀስ ብሎ በክብ ፊቷ ላይ ይፈስ ጀመር።





“ታዲያ ግን ለምንድነው ከዚያ በኋላ በትክክል መራመድ ያቃተሽ” ብሎ እንደገና ጥያቄውን በመገረም አቀረበ። “በትክክል አለመራመድ ይቻላል ግን?” እኔ ግን አረማመድሽን በጣም ነው የወደድኩት። በምትራመጂበት ጊዜ ዳሌሽ በእርጋታ ነው የሚንቀሳቀሰው፤ ይሄ ደሞ ቆንጆ ነው። በዚህ ጊዜ ድንቅነሽ ሳቀች፡፤ “አንዳንድ ጊዜ መራመድ በጣም ያስቸግረኛል፤ አንዳንድ ጊዜ እንዲያውም ፍጹም የማይቻል አይነት ነገር ይሆንብኛል” ብላ ፊቷን ቅጭም አደረገችው። ኤዲ ሲያስብ ሲያስብ ቆየና በድንገት አንድ ሐሳብ መጣለት፡- “ይሄ እኮ ግልጽ ነው፤ አንድ ምርኩዝ ያስፈልግሻል!” አላት። የምን ምርኩዝ? ብላ በጥያቄ መልክ አየችው ድንቅነሽ። ኤዲ “ስትራመጂ ለመራመድ የሚረዳሽና የምትደገፊው አይነት መመርኮዣ ነው” በምትራመጂበት ጊዜ ሚዛንሽን እንድትጠብቂና ቶሎ እንዳይደክምሽም ይረዳሻል። እንዲያውም እዛ ውጪ ጓደኛዬ ሌዎን እየጠበቀኝ ነው። እሱ ለመራመድ የሚረዳ ከዘራ አለው። በደስታ ያውስሻል ብዬ እገምታለሁ አለና፤ እህስ እንዴት ነው? ብሎ ጠየቃት፡ ፡ ሌዎን ጋር እንሂድና እንጠይቀው? የድንቅነሽ አይኖች እንደ አልማዝ እንደገና ያንጸባርቁ ጀመር። “እሺ እሺ” እያለችና ወደ ላይ እየዘለለች በደስታ ዳሌዋን እያወዛወዘች ደረጃውን መውጣት ጀመሩ።



# ቆሎ ይዞ ወደ ታላላቆቹ ፈላሳፎች

“ዋው፤ በጣም ይጣፍጣል፣ ደረቅ ያለና በቅመም ያበደ ነው”: : ይጣፍጣል አይደል? ሴዎን ትንሽ ልጨምርልህ? ብላ ማክዳ ጠየቀችው። እኔም አዎ በደስታ ብዬ መለስኩላት፤ አፌ በግማሽ በምግብ ተሞልቶ። ኤዲን እየጠበቅን በነበረበት ሰዓት ማክዳ በፌስታል ይዛ የነበረውን የሚቆረጠም ነገር አውጥታ ሰጥታን ነበር። ብራኢሊም “በእውነት በጣም ነው የሚጣፍጠው” አለ። “ከጥራጥሬ የተሰራ ነው፤ በትልቅ ምጣድ ላይ ወርቃማ ቡኒ ቀለም እስኪመስል ድረስ ተቆልቶ ነው የሚዘጋጀው” ብላ ማክዳ አስረዳቻቸው። ቢያስፈልግ በጣፋጭ መልኩ ካስፈለገም በጨው ተደርጎ መመገብ ይቻላል። አልፎ አልፎ አነስተኛ የሆነ ነገር መብላት ለሚፈልግ በጣም ጣፋጭ ምግብ ነው። “ትክክል፤ እኔ ይህ ቆሎ ሊበቃኝ አልቻለም”: : “ምንድነው የምትቆረጥሙት? እኔ እኮ አልደረሰኝም!” ብሎ ኤዲ በድንገት አጠገባችን ደርሶ አጉረመረመ። “ይሄውልህ ቆሎ ነው” ሲል የሆነ ወዳጃዊ የሆነ ሆኖም ግን ሰምቼው የማላውቀው ድምጽ ከኤዲ ጀርባ ሰማሁኝ። ተንቀሳቃሽ ወንበሬ ላይ ተቀምጬ እንደ ልቤ መንቀሳቀስ ስለማይመቸኝ አንገቴን ወደ ፊት አስግጌ ጭንቅላቴን ወደ ኋላ አዙሬ እያወራ ያለው ማን እንደሆነ ለማየት ሞከርኩኝ። ሆኖም ግን ሊሳካልኝ አልቻለም። የማክዳና የአቢ የመደነቅ ስሜት ከፊታቸው ላይ ይታየኝ ነበር። አይናቸውን አፍጥጠው ከኤዲ ጋር አብሮ የመጣውን ሰው ያዩ ነበር።

አቢ እየተንተባተበ “ድድድድደድ ይይጎ ዕኮ...” አቢ መናገር አቅቶት ሲንተባተብ አያለው ብዬ አስቤ አላውቅም ነበር። ማክዳም ከአፏ አንድም ቃል ማውጣት አልቻለችም ነበር። የሁለቱን በጣም የመገረም ስሜት የሚነበብበት ገጽ ልብ ያላለው ብራኢሊ “ኤዲ፤ ማንነው ይዘህ የመጣኸው? ጓደኛህን አስተዋውቀና! እያለ ይጠይቃል: : እሱም “እሺ እሺ” አለና፤ እሷ ድንቅነሽ ትባላለች፤ እናም ትንሽዬ ጦጣ ናት ብሎ አስተዋወቃቸው። የተዋወቅነው በህልሜ ነው፤ እናም ዛሬ ሙዚየሙ ውስጥ እንደገና ተገናኘን፤ ከኛ ጋር ትንሽ መቆት ፈልጋ ነው የመጣችው፤ ችግር የለውም አይደል? ብሎ ጠየቃቸው። ኤዲና ድንቅነሽ ፊታቸው በፈገግታ ተሞልቷል።



“አይ ችግር የለውም፤ እንኳን ደህና መጣሽ ድንቅነሽ ብላ ማክዳ ለትንሿ ጦጣ ቆሎ ያለበትን ፌስታል ከፊት አርጋ አቃበለቻት። “እሺ እሺ” ከፈለጋችሁ ድንቂ ብላችሁም ልትጠሩኝ ትችላላችሁ ብላ ከቆሎው ዘገን አድርጋ አፏ ውስጥ ጨመረችና እየቆረጠመች ተቀላልቀለቻቸው። “ሴዎን” ብሎ ኤዲ ጠራኝና “ምርኩዝህን ሻንጣህ ውስጥ ይዘህዋል አይደል” ብሎ ጠየቀኝ። ለድንቂ ልታውሳት ትችላለህ ለማለት ፈልገህ ነው? ድንቂ በአንድ ወቅት አደጋ ደርሶበት ነበር: : ስለሆነም በምትራመድበት ጊዜ ቶሎ ይደክማታል”። ትንሽ አሰብ አደረኩና፡- በእርግጥም ምርኩዙን ብዙም አልጠቀምበት፤ ምርኩዙ የሚያስፈልገኝ ከአቅም በላይ የሆነ ነገር ሲያገጋጥመኝ ብቻ ነው: : በተለይ ደሞ ይህንን በኤሌክትሪክ የሚሰራ ተንቀሳቃሽ ወንበር ካገኘሁ ጀምሮ ምርኩዙን ተጠቅሜበት አላውቅም አልኳቸው: : ድንቂ፤ አቢ ምርኩዜን ሰጣትና በሱ እየተረዳች ትንሽ ከተራመደች በኋላ ፊቷ በደስታ ተሞላ። አንቺን ማስደሰት በመቻሌ በጣም ደስታ ይሰማኛል አልኳት። ከዛም አዲስ ተጨማሪ ጓደኛ ማግኘታችን እንዳስደሰተው በሚያሳብቅ መልኩ ሆኖ “በሉ እንግዲህ፤ ምንድን ነው የምትጠብቁት እንንቀሳቀሳ። ማክዳ ምንድን ነው ገና ያላሳየሽን ነገር አለ ብራኢሊ። ከዛም ሁላችንም ወደፊት ተንቀሳቀስን።



የተወሰኑ ደቂቃዎች በእግራችን ከተጓዝን በኋላ ወደ አንድ በተለያዩ ቅርጻ ቅርጾች ወደተዋበ በር ጋር ደረስን። “አው፤ ምን የሚባል ቤተ መንግስት ነው?”ብሎ ኤዲ ጠየቀ። ድንቂም በመገረም ውስጥ ሆና ነበር በመግቢያ በሩ ላይ ከድንጋይ የተሰሩትን የአንበሳ ቅርጾች የምትመለከተው። “የተወደዳችሁ ጓደኞቼ ይሄ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ነው” እኔም በየቀኑ ለማለት በሚያስደፍር ሁኔታ ወደዚህ ቦታ እመጣለሁ ብላ ማክዳ በኩራት ውስጥ ሆና አስረዳችን፡
፡ ብራኢሊ “ሙሉ ለሙሉ ትክክል አይደለችም ማለት አይቻልም” ኤዲ አለና ሞባይል ስልኩን አውጥቶ በእጆቹ ይዞ አዘጋጀ። “ዋናው ሕንጻ ከብዙ አመታት በፊት ንጉስ አፄ ሐይለ ስላሴ እንደ ቤተ መንግስት ይጠቀሙበት ነበር” አለ ብራኢሊ። “ትክክል ነው” ብላ የብራኢሊን ሐሳብ እንደምትስማማበት ከገለጸች በኋላ ለእኔ በጣም ዋና ነገር ነው ብዬ የማስበውን አንድ ሌላ ነገር ደሞ ላሳያችሁ ብላ ከመግቢያው በር በጎን በኩል ወዳለ አንድ ትልቅ ባነር ጠቆመችን፡
፡ በላዩ ላይ በትልቁና ለማንም ሰው በግልጽ በሚታይ ሁኔታ “ታላላቅ ሊቆች ሰለ ሰው ልጆች ችሎታ እንጂ ሰለ ሰው ልጅ የተፈጥሮ ውሱንነት አይጨነቁም” የሚል ጽሁፍ በትልቁ ተጽፎበት ይታያል።



ኤዲም “ይሄ ግን በጣም ረጅም ዓርፍተ ነገር ነው” ብሎ ተናገረ፡
፡ እያንዳንዱን ቃላት በጭንቅላቱ ውስጥ ሲያብላላቸው ይታየኝ ነበር። ትንሹ፤ ብረት ለበሱ ጓደኛዬ ብሎ አቢ ማብራራቱን ጀመረ “ይሄ ማለት የሰው ልጅ ያለበት የአካል ወይም የመንፈስ ውሱንነት ዋናው ጉዳይ አይደለም ዋናው ነገር አንድ ሰው አንድን ነገር እንዴት ጥሩ አድድጎ ይሰራዋል የሚል መሆን አለበት ማለት ነው” አለ። ኤዲም ትከሻውን ሰበቅ እንደማድረግ ብሎ “ይሄማ በትክክል አምክንዮታዊ ነው” አለ። ሆኖም ግን በእንደዚህ ከባድ በሆነ ዓርፍተ ነገር መገለጽ አልነበረበትም አለ።
እኔ በጣም ነው ያስደነቀኝ። በመጀመሪያ ደረጃ፤ የእኛ ኤዲ የእኔ በተሽከርካሪ ወንበር ወይም ደሞ ብራኢሊ የአይነስውራን ዱላ መጠቀሙ ልዩነት የማይፈጥረበት መሆኑ።
13በማስቀጠልም ይህ ባነር ከዩኒቨርሲቲው በር ላይ መሰቀሉና ሁሉም ሰው ይህንን ታላቅ መልዕክት ማየት መቻሉ የሚደነቅ ነው። ማክዳ ወደ እኔ መጣችና፡-.እዚህ እኛ ሐገር ኢትዮጵያ ውስጥ ከአካል ጉዳተኞች ጋር ያለን ግንኙነት ብዙም የተለመደ አይደለም፡
፡ ለረጅም ዘመናት ርዕሱ ራሱ አይነኬ አይነት ጉዳይ ነበር።



አንድ ሰው የአካል ጉዳት ካለበት የእለት ተዕለት ህይወቱን ሊያቀልለት የሚችል የሚታገዝበት መሳሪያ ካለመኖሩም ባሻገር፤ በተቃራኒው መንገድ ደሞ እነኚህ ያሉበት ችግሮቹ በጣም በርካታ ከመሆናቸውም ባሻገር እነደዚህ አይነት ሰው በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት አልነበረውም። እንዲያውም እስካሁን ድረስ የአካል ጉዳት ያለበት ሰው እራሱን ደብቆና ከማሕበረሰቡ ተገልሎ ነበር የሚኖረው ብላ በአዘነ መንፈስ ውስጥ ሆና ተረከችልን። “ሆኖም ግን ባለፉት ዓመታት ብዙ ነገር ተለውጧል። ሁሉንም አካታች የሆነ ስርዓተ ሕይወት እየተጀመረ ነው። በዚህ ዩኒቨርሲቲ ውስጥም ብዙዎቹን ነገሮች መማር ይቻላል፡ ፡ ለዚህም በጣም ኩራት ይሰማኛል። ወደ ፊት የሚያንቀሳቅሱ ትንንሽ እርምጃዎች ወደ ኋላ ከሚመለሱ ረጃጅም እርምጃዎች የተሻሉ ናቸው። ׀ማክዳ አይን ውስጥ የሚያበራ ሳቅ እየሁና አጸፌታውን በፈገግታ መለስኩላት። ከዛም በድንገት ሞባይል ስልኳ ደወለ፤ ትንሽ በስልኩ ከተነጋገረች በኋላ ሁላችንንም አንድ ላይ ሰበሰበችንና፡- “ጓደኞቼ መሄድ አለብን። ካሽንና የአቢ እናት ከጥቂት ጊዜ በኋላ ወደ ተቀጣጠርንበት ቦታ ይደርሳሉ አለች። የት ነው የቀጠሮ ቦታችን? ብላ ለማወቅ በፈለገ ጉጉት ውስጥ ሆና ድንቂ ጠየቀች፡ ፡ አቢና ማክዳ እየተሳሳቁ “ቦታው አንድ በጣም አስደናቂ ስፍራ ነው” ብላ ማክዳ መለሰች።.





# ዘመን የማይሽረው ጓደኝነት

ከሚኒባሳችን ውስጥ ሁላችንም ወረድን። ምሳ ሰዓት አካባቢ ወደ አንድ ትልቅ ሕንጻ ቅጥር ግቢ ስንደርስ ጸሐይዋ መሐል ሰማዩ ላይ ደርሳለች። ገና ሩቅ እያለን የሰዎች ሁካታና ጫጫታ በየመሀሉ ደሞ ሞቅ ደመቅ ያለ ሳቅ እንዲሁም ደስ የሚል ጣእመ ዜማ ይሰማል። ብራኢሊ “የት ነው ያለነው?” ብሎ ጠየቀ፤ እኔም ብሆን ማክዳና አቢ ወደ ምን አይነት ቦታ እየወሰዱን ያለው ብዬ ለማወቅ ጓጉቼያለሁ። በአንድ ረጅም ኮሪደር ባለው በጣም ትልቅ ሕንጻ ውስጥ አልፈን በድንገት አንድ የትምሕርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ እራሳችንን አገኘነው። አቢ በዙሪያችን ከበውን የሚንጫጩት ተማሪዎች እንዲሰሙት በማሰብ ጮክ ብሎ “ሄይ ሄይ ጓደኞቼ ይህ በጣም ድንቅ የሆነ ቦታ ነው፡- የጀርመን ቤተክርስትያን ትምሕርት ቤት ነው” አለ። ኤዲ አይኑን ከወዲያ ወዲህ እያንከራተተ “ትምሕርት ቤት እኮ ደባሪ ቦታ ነው” አለ። ማክዳ ቀበል አድርጋ “እዚህ ግን እንደዛ አይደለም” አለችው። “ይህ ትምህርት ቤት ለሁሉም ሰዎች የሚሆን ቦታ ነው”። እዚህ ማንኛውም ተማሪ፤ የአካል ጉዳት ያለበትም የሌለበትም ሁሉም በጋራ የሚማሩበት ትምሕርት ቤት ነው አለች።





አካባቢዬን ልብ ብዬ
መመልከት ስጀምር ማክዳ ምን ለማለት እንደፈለገች በደንብ
ገባኝ። በአካባቢው በተንቀሳቃሽ ወንበር የሚንቀሳቀሱ ተማሪዎች
ሌሎች ተማሪዎች እየገፏቸው ይታያሉ። አንዷት አይነ ስውር ተማሪ
ከጓደኛዋ ጋር አንድ ላይ ሆና ትታያለች። ተማሪዎቹ በትምሕርት
ቤቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ በእግራቸው እየተጓዙ እየተሳሳቁ ያወራሉ፡
፡ እዚህ ያለው አጠቃላይ ድባብ ሞቅ ያለና የሚያስደስት አይነት ነው፡
፡ ማክዳ ማብራሪያዋን በመቀጠል “እዚህ ትምሕርት ቤት ውስጥ
የሚማሩት ወይ በጣም ድሐ የሆኑ ተማሪዎች አልያም ደሞ የአካል
ጉዳት ያለባቸው ብቻ ናቸው” አለች። በቂ ገንዘብ የሌላቸው በርካታ
ወላጆች ልጆቻቸውን ትምሕርት ቤት አይልኳቸውም። በተለይም
ደሞ የአካል ጉዳት ያለባቸው ልጆች ከሆኑ ደሞ፤ ልጆቹ የሚረዱበት
የራሳቸው የሆነ የተለያየ መሳሪያ ስለሚያስፈልጋቸውና ይህ ደግሞ
በሌሎች ትምሕርት ቤቶች ስለማይገኝ በጣም አስቸጋሪ ይሆንባቸውል፡
፡ እዚህ ግን ሁሉም ነገር የተለየ ነው ብላ ንግግሯን አጠቃለለች።
ልክ ምሳ ሰዓት ላይ ነበር የደረስነው። እያንዳንዱ ተማሪ አንድ
ዳቦ፣ አንድ ሙዝና ወተት ይሰጠዋል። እኛም የትምህርት ቤቱ
ቅጥር ግቢ አንድ ጥግ ላይ ተቀምጥን ምግባችንን አጣጣምን፡
፡ ጥቂት ተማሪዎች ኳስ ይዘው ተጠጉን። ከዛም “ኳስ አብረን
እንጫወት?” ብለው ጠየቁን። ኤዲና ድንቂ በጣም ደስ ብሏቸዋል፡
፡ ሁለቱም ብዙም ሳያንገራግሩ ተስማሙ። እኔ ነገሮችን ልብ
ሳልል በአጭር ቅጽበት ውስጥ ኤዲ በጎሎቹ መሐል በረኛ
ሆኖ ቆሞ ድንቂ ደሞ ኳሷን ስታቀብል አየሁ። መደገፊያ ከዘራ
ያስፈልገኛል የሚለው ነገር ምንም አላስጨነቃትም ነበር።
እኔም አብሬ ለመጫወት ድፍረት ብጤ በማጣቴ የተነሳ እራሴ
በራሴ ትንሽ በስጨት እንደማለት አደረገኝ። አንዳንድ ጊዜ
በተንቀሳቃሽ ወንበር ላይ ስለተቀመጥኩ ሌሎች ሰዎች ሁሉ



የሚያደርጉትን ነገር ለማድረግ ፍርሐት ሸብቦ ይይዘኛል
ማክዳ፤ እኔ ኳስ ሲጫወቱ እንዴት በጉጉት እየተመለከትኩ
እንደሆነ ልብ ብላለች። ስለሆነም “እህስ” እንዴት ነው አንድ ጎል
ብታገባ ምን ይመስልሀል? አለችኝ። እኔም አፈር እንደማለት ብዬ
አንገቴን በመነቅነቅ ፍላጎቴን ስገልጽላት ተሽከርካሪ ወንበሬን
እየገፋች ወደ ሜዳው አስገባችኝ። ብራኢሊ ከአቢ ጋር ሙጭጭ
ብሎ አለቅም ብሏል፤ ሁለቱ የሆነ ነገራቸው በትክክል እንደገጠመ
ያስታውቃል። ከጀርመን ቤተክርስትያን ትምሕርት ቤት ተማሪዎች
ጋር በጋራ ሆነን ደስ የሚል የኳስ ጨዋታ ጊዜ አሳለፍን።
ከጫወታው በኋላ ሲጠበቅ የነበረው ጊዜ ደረሰ። የአቢ እናትና ካሸን
ወደ ጀርመን ቤተክርስትያን ትምሕርት ቤት መጡ። በሚቀጥለው
ዓመት እርሱም እዚህ ትምሕርት ቤት ይገባል። እሱም በስተመጨረሻ
መጻፍና ማንበብ ልማር ነው ብሎ ተደስቷል። አቢ ወደ አንድ
እረፍት ሲወጡ ወደሚቀመጡበት ክፍል ወሰደንና ቆሎ እየበላን
ተሰብስበን ተቀመጥን። ማክዳ እኔ ከጀርመን ሐገር ይዤ የመጣሁትን
ተጣጣፊ ተንቀሳቃሽ ወንበር ከሚኒባሱ አውርዳ ይዛው መጣች፡
፡ ካሸን እናቱ እየረዳችው ወንበሩ ላይ ተቀመጠ - ይሆነዋል! የካሸን
አይኖች ሲያበሩ ይታያሉ። አቢና እናቱ ተደስተዋል።”ዋው እንዴት ደስ
ይላል”፤ ሁላችንም ደስ ብሎናል። የካሸንስ እናት “ይህ ተንቀሳቃሽ
ወንበር ሁላችንንም ይረዳናል” አሉ። እኔም ተጣጣፊ ተንቀሳቃሽ
ወንበሬ ይህን ያህል ደስታ መፍጠር በመቻሉ ደስታ ተሰምቶኛል።



አንድ ላይ ሆነን የትምሕርት ቤቱን ክፍሎች ጎበኘን። አቢ ከአሁን ቀደም እዚሁ ትምሕርት ቤት ተምሮ ስለነበር የሚያስጎበኘን እሱ ነው። የታችኛው ደረጃ ላይ ያሉት ክፍሎች የአካል ጉዳተኛ ሆነው በተንቀሳቃሽ ወንበር ለሚንቀሳቀሱ ወይም ሌላ የመርጃ መሳሪያ መጠቀም የሚገባቸው ተማሪዎች ያለ ምንም ችግር እንዲጠቀሙባቸው ተደርገው ነው የተሰሩት። በአይነስውራን ጽሁፍ (ብሬል) በርካታ መጽሕፍቶች መኖራቸው ብቻ ሳይሆን በየክፍሎቹ ግድግዳዎች ላይ በብሬል ጸሁፍ የተጻፋ የመማሪያ ጥቁር ሰሌዳዎች ተሰቅለዋል። ብራኢሊ በጣም ከመገረሙ የተነሳ በየክፍሉ እየገባ ይዳስሣቸዋል። ማክዳ እዚህ ትምሕርት ቤት ውስጥ በኢትዮጵያ ዙሪያ እንዳለው ሁሉ በርካታ አይነስውራን ተማሪዎች እንዳሉ ገለጸችልን። ስለሆነም ልዩ ድጋፍ ለሚሹ አይነ ስውራንና በደንብ ማየት ለማይችሉ በብሬል የተጻፋ መጻሕፍት ያሉት አይነ ስውራን ሊጠቀሙባቸው የሚችሉት መጻሕፍት ቤት እንዳለውም አስረዳችን። እኔ፤ ሆኖም ግን በተንቀሳቃሽ ወንበርና በምርኩዝ ወይም ከዘራ የሚንቀሳቅሱ ተማሪዎችም እንዳሉ ይታዩኛል ብዬ ጠየቅሁ። ሌዎን "ትክክል ነህ" ብሎ አቢ መለሰ። አያይዞም ይሕ ት/ቤት ማንኛውም ሰው ሊማርበት የሚችል ት/ቤት ነው። ማንኛውም እገዛና ድጋፍ የሚያስፈልገው ተማሪን በደስታ ነው የሚቀበለው። እዚህ ያለነው ሁላችንም በራሳችን መንገድና እርስ በእርሳችን እየተረዳዳን አንዱ የሌላውን ችግር እየተረዳ ነው የምንኖረው አለ "አንዱ የሌላውን ችግር እየተረዳና አንድ ላይ ሆነን መኖር!" ሲሰሙት በጣም ደስ ይላል ብዬ አሰብኩና ይህንን ሓሳብ የሕይወቴ መሪ ቃል ለማድረግ ወሰንኩ። እንደ እኔ ሐሳቡ ድንቅ ነው። በተለይ የወደድኩት ደሞ ስራቸውን በቡድን መስራታቸውን ነው "በመጀመሪያው የትምሕርት ቀን እያንዳንዱ ተማሪ አንድ ጓደኛ ይመደብለታል - ይህ ጓደኛው አዲሱን ተማሪ የሚያግዘው ሰው ነው። ማክዳ ሳቅ እያለች አቢን በሚያማልል እይታ ታየዋለች። "አቢ እንግዲህ ተዋወቅን አይደል?" አቢ አንገቱን ከነቀነቀ በኋላ ያብራራልን ገባ። "እዚህ ማንኛውም ሰው ሁል ጊዜ ለሁለት ለሁለት ነው መሆን ያለበት" አንድ የአካል ጉዳት ያለበት ተማሪ ሌላ የአካል ጉዳት የሌለበት ተማሪ ጓደኛ ይኖረዋል። እርስ በርስ ይረዳዳሉ።፤ ማክዳና እኔ ስምንት አመት ሙሉ ጓደኛሞች ነበርን። "እስከ አሁንም ድረስ ጓደኛሞች ነን" አለ። ማክዳ እየሳቀች የአቢን እጅ ያዘች። ኤዲ እየተጣደፈ "ቆይ ቆይ" አለ። አስከትሎም በናንተ ቡድን ውስጥ የአካል ጉዳት ያለበት ማነው ብሎ ጠየቀ። ኤዲ እውነቱን ነው: : ማክዳን ሳውቃት በጣም ቆይቻለሁ፤ እናም እስከማውቃት ድረስ እሷ ምንም አይነት የአካል ጉዳት እንደሌለባት እርግጠኛ ነኝ። ቢሆን ኖሮ



እስካሁን ድረስ ትነግረኝ ነበር። አቢ እንደ ማፈር ብሎ መሬት መሬቱን ማየት ጀመረ። "አዎ፤ ጓደኞቼ እስካሁን ድረስ አልነገርኳችሁም። እኔም የአካል ጉዳተኛ ነኝ። በደንብ መስማት አልችልም። ማለትም አንደኛው ጆሮዬ አይሰማም"። "ይሄ ሊሆን አይችልም!" አለ ኤዲ አምልጦት እኔም በጣም ነው የተገረምኩት። "ግን ምንም አይታወቅብህም": : አቢም "እውነት ነው" በማለት መለሰ። በሚያሳዝን መልኩ እንደዚህ ያለው የአካል ጉዳትም ትልቅ ችግር ነው፤ ለሰው የሚታይ አይደለም። ስለሆነም ሌሎች ሰዎች ሊረዱኝና ሊያግዙን አይቻላቸውም: : ብዙ ጊዜ ልብም ሳይሉኝ ያገሉኛል"። እንደዛ እብድ የነበረው አቢ በድንገት ጸጥ ብሎ ያሰላስል ጀመር።





በዚህን ጊዜ በድንገት የሆነ ነገር ለኔ ተገለጸልኝ። አቢ ብዙ ጊዜ በጣም ጮክ ብሎና በሚረብሽ መልኩ ነበር የሚያወራው። “እንግዲህ እኔ ደንቆሮ ነው ሲባል በሚባል ደረጃ ለመስማት ስለምቸገር ሳወራ፤ የማወራው ለራሴ እንዲሰማኝ ስል ጮክ ብዬ ነው፡ ፡ በተጨማሪም የምለውን ነገር ሌሎች እንዲረዱኝ በማሰብ በሓይል ወዲያ ወዲህ እየተወራጨሁ ነው የማወራው” አለ ይቅርታ እየጠየቀ ያለ በሚመስል መልኩ። ስለሆነም ብዙ ጊዜ “ሌሎች ሰዎች ግራ ሲጋቡ አያለሁ”። “አህ ተዋቸው ዝም ብለህ ነው”፤ “እንዲያውም በጣም አሪፍ ነው፤ አንተ በጣም ተጫዋች ነሕ፣ ሁል ጊዜ ደስተኛ ነህ እናም ጠንካራም ነህ” አለ ኤዲ። እንግዲህ እኛም ጓደኛሞች ሆንን ማለት ነው አለ ኤዲ፡ ፡ ኤዲ የሚችለውን ሁሉ ወደ ላይ ዘለለና የሕይወት ዘመን ጓደኛሞች! ብሎ ጮኸ፤ ሁላችንም ተሳሳቅን። አቢም ሳቀ። አሁን ሚስጥሩን ስላካፈለን ቅልል ብሎታል። እኛም አምኖ ስላጫወትን ደስተኛ ሆነናል።



# የማይረሳ ግንኙነት

እኛ ጨዋታችንን ይዘን ሳለ ትንሹ ካሽን በአዲሱ ጋሪ ላይ ሆኖ አቧራው ካለበት አካባቢ ለቅቆ ሄደ። በስተመጨረሻም በራሱ መንቀሳቀስ በመቻሉ እየተደሰተ በሚቀጥለው የትምሕርት ዘመን የሚገባበትን የትምሕርት ቤቱን ዙሪያ ገባውን እየተዘዋወረ መመልከት ጀመረ። ተማሪዎቹ በትምሕርት ሰዓትና በእረፍት ጊዜያቸው የሚጠቀሙባቸውን በትምሕርት ቤቱ ጓሮ በኩል ያለውን ስፍራ፣ አረንጓዴውን የመናፈሻ ቦታ፣ የአካል ጉዳተኞች ለሆኑትም ሆነ ላልሆኑት የሚያገለግለው የጋራ መጫወጫ ቦታን እየተዘዋወረ ማየት ቻለ። በተለይም ደሞ በተንቀሳቃሽ ወንበር የሚንቀሳቀሱትም ሆነ በእግራቸው የሚሄዱት ተማሪዎች ሁሉም በጋራ የሚነዷት ትንሿ የምትሽከረከረው መጫወቻ ቀልቡን ሰባዋለች።





እሱ ተጠንቅቆ በምትሽከረከረዋ መጫወቻ ለመሽከርከር ሲዘጋጅ ሌላ የሆነ ሰው መጥቶ አጠገቡ ቁጭ አለ፡፡ “ማን ነህ አንተ ደሞ? እዚህ አይቼህ አላውቅም” የሚል የሚያስገመግም ድምጽ ሰማ፡፡ ዞር ብሎ ሲመለከት  ቀይ ሆኖ የሚያበራ አይን ያላት አንዲት ጅብ ከአጠገቡ ሲትቀመጥ አየ፡፡ ካሸንም ደንገጥ ብሎ በሚንቀጠቀጥ ድምጸት፡- “ካሸን እባላለሁ፤ ለአካባቢው አዲስ ነኝ” አለ “አሃአሃአሃ፤ ለአካባቢው አዲስ ነኝ፤ አስቴር እባላለሁ፡፡ እንዴት አይነት አሪፍ የሆነ ተንቀሳቃሽ ወንበር ነው ያለህ ባክህ? ሲያዩት በጣም ያምራል፡፡ እዚህ ብቻህን ነው ያለህው?” እያለች አንበሲቷ ተንቀሳቃሽ ወንበሩን በጥንቃቄ ታያለች፡ ፡ “ሄይይ ሀሎ አስቴር፤ ትክክል ነው፤ መንቀሳቀሻ ወንበሩ አዲስ ነው፡ ፡ ገና ዛሬ ነው የተሰጠኝ፡፡ ግን አሁን ተመልሼ ወደ ትምሕርት ቤት ሕንጻ መሄድ አለብኝ፤ እናቴና ወንድሜ ይጠብቁኛል”፡፡ ካሸን በጣም ፈርቷል፤ ስለሆነም ከሚሽከረከረው መጫወቻ ላይ ቶሎ ወርዶ የተቀሩት ወዳሉበት በቶሎ ለመመለስ ፈልጓል፡፡ ሆኖም ግን ተንቀሳቃሽ ወንበሩን ገና ብዙም ስላልለመደው ወደ ኋላ መምንዳቱ ትልቅ ፈተና ሆነበት፡፡



“አሕ፤ ትንሽ ቆይ፡፡ መጣሁ ቆይ ልርዳህ” ብላ ጅቧ ተጠጋችው፡ ፡ ልክ እሷ ወደ ኋላ መሄጃውን ለካሸን ልትከፍትለት ስትሞክር የአቢ ድምጽ ሲይስገመግም ተሰማ፡፡ “ካሸን፣ ካሸሸሸን፤ የት ነው ያለህው?” በዚህን ሰዓት አስቴር በፍጥነት ከመጫወቻው ላይ ዘላ በመውረድ ከመጫወቻው ቦታ አጠገብ ካለው ዛፍ ስር ተደበቀች፡፡ ካሸንም ወንድሙን አቢን ሲያየው ከመጫወቻው ላይ እንደሚያወርደው ተስፋ አርጎ ተደሰተ፡፡ ወደ ትምሕርት ቤቱ ሕንጻ እየሄዱ ባለበት ሰአት ካሸን አንድ ጊዜ ዞር ብሎ ወደ ኋላው ሲመለከት የአስቴርን የሚያበሩ ቀያይ አይኖች ከዛፎቹ ኋላ ተደብቆ አየ፡፡ በጀርባው በኩል ላብ ወደ ታች ሲንቆረቆር ተሰማው “ለጥቂት ነው የተረፍኩት” ብሎ አሰበ፡፡

# ኤዲ! ተነሳ

ከእንቅልፌ ስነቃ ገና በጣም ጠዋት ነበር። ሌሎቹ ገና ሳይነቁ ቶሎ ቶሎ ብዬ ልብሴን ለበስኩና ጥርሴን ፋቅሁ።ትናንት ማታ በጣም አምሽተን ነበር። አቢ ወንድሙንና እናቱን ሊሸኛቸው አብሮ ሄዷል፡ ፡ የተቀረነው በእንጦጦ ተራራ ስር በሚገኘው የማከዳ አረንጓዴ ስፍራ ውስጥ የሚጣፍጥ እንጀራ እየበላን እየተዝናናን ነበር።

እስከ እኩለ ሌሊት ድረስ እርስ በርሳችን እየተጫወትን፣ እየሳቅንና እየተቀላለድን ነው ያሳለፍነው። የተለያየ ሙዚቃም ስንጫወት ነበር። ጸሐይዋ በእንጦጦ ተራራ ላይ ስትፈነጥቅ ከእንቅልፌ ተነስቼ በረንዳው ላይ ወጥቼ ወደ ውስጥ ንጹሕ አየር እተነፍሳለሁ። አቤት የጠዋቷን ንጹሕ አየር መሳብ እንዴት ያስደስታል። ጠዋት ላይ ያለው ጸጥታ ውስጥ ድረስ ዘልቆ ይሰማል። ከውስጥ በኩል ለየት ያለ ድምጽ ይሰማል። "ሆፕ ሆፕ ሄይ ሄይ - ከአልጋው ላይ ውረድ" የሚል ድው ድው የሚልና ሲጢጢ የሚል ድምጽ፤ ድንቂ ትዘፍናለች። ከቤቱ ጥግ ላይ ሆኜ ወደ ውስጥ ስመለከት ኤዲ አልጋ ላይ አንድ እብድ ስትዘል አየኋት። ሎሆሆሆስ ተንስ አንተ አንኳራፊ! ትንሹ የኤሊው ጭንቅላት ከብርድ ልብሱ ውስጥ ቀስ እያለ መውጣት ጀመረ። ኤዲ ያዛጋል ይንጠራራል። ስንት ሰዓት ሆኖ ነው? ብሎ ጠየቀ። ዲንቂ "ያፈለገው ይሁና!" እያለች ትጮሃለች፤ ፡ውጪ እኮ ሰፊውና ትልቁ አለም ይጠብቀናል!" "አአአርርርር፤ እኔ ደክሞኛል። ትንሽ መተኛት እፈልጋለሁ" እያለ። ኤዲ ተነጫነጨና በብርድ ልብሱ ጥቅልል ብሎ ተኛ። ድንቂ በመብራቱ ላይ ወደ ላይ እየወጣችና በአልጋው ትራስጌ አናት ላይ ተንጠልጥላና የኤዲን ብርድ ልብስ እየጎተተች "ኤዲ እንቅልፋም ኤዲ እንቅልፋም! እያለች ትጫወታለች፡ ፡"ሄይ፤ ተይ እንጂ" ብሎ ጮኸ ኤዲ። እሷም ባይሳካላትም ብርድ ልብሱን ለመግፈፍ በተደጋጋሚ ትሞክራለች። ኤዲም በድንቂ በምንም አይነት ሊያዝንባት አልቻለምና በስተመጨረሻ መሳቅ ጀመረ። "እሺ፤ እንቀጥል አይደል" አለና መንቀጥቀጥና መቃተት ጀመረ። ከዛም ከአልጋው ላይ ተስፈንጥሮ ተነሳና ለሁላችንም ቁርስ እያዘጋጀች የሚሆነውን ሁሉ እየሳቀች እንደ ቲያትር ስትከታተል የነበረችው ማከዳ ላይ ቀይ ኮፍያውን አጠለቀላት። ከዚህ ቀጥሎም የጠዋቷን ጸሀይ እያጣጣምን የሚጣፍጥ ሙዝ በትልቅ ብርጭቆ ወተት ጠጣን። በድንገት ንቅትቅት ያለውና በፊቱ ላይ ያለውን ጺሙን



በወተት ያራሰው ኤዲ "ዛሬ ምንድን ነው የምናደርገው" ብሎ ጠየቀ?። "እህ ኤዲ!" ብሎ ብራኢሲ በመደነቅ መለሰለት። "እረሳኸው እንዴ? ማከዳ እኮ ትናንትና የጀርመን ቤተክርስትያን ትምህርት ቤት ሳለን ከአንድ ጓደኛዋ የብሔራዊ የአይነ ስውራን ማህበር ጎረቤታሞች እርስ በእርስ የሚገናኙበት በአል እንዳለው ነግሯት ነበር። አቢና ካሸንም አብረውን ለመሄድ ፈልገዋል። ኤዲ በጭንቅላቱ ውስጥ ነገሮቹ ሁሉ እንደ ጠረጴዛ ኳስ ወዲያ ወዲህ ሲሉበት አስተዋልኩት፡ ፡ በስተመጨረሻም "ትክክል!" ብሎ ጮኸ።





በዚህን ጊዜ የአቢ ሚኒባስ ወደ ማክዳ ቤት የሚያደርሰውን ዳገት ለመውጣት ስትንኮራኮር ተሰማን። በሓይል ክላክስ ነፍቶና ተንገጫግጮ በሐይለኛው አቧራ አቡንኖ ቆመ። ወሩ የካቲት ሲሆን፤ ኢትዮጵያ ውስጥ የክረምቱ ጊዜ እየተቃረበ ያለበት ጊዜ ነው። መሬቱ በጣም ደርቆ አቧራማ ሆኗል። የአቧራው ጉም ሲገፈፍ አቢን መኪናው አጠገብ ቆሞ እጆቹን ሲያውለበልብ አየነው። ደስ የሚል ሸሚዝ ለብሷል። ትንሹ ካሸን ፊቱ በሳቅ ተሞልቶ በመስኮት በኩል ብቅ ብሏል። የመንቀሳቀሻ ወንበሩ በመኪናው አናት ላይ ታስሮ ይታያል። ሁለቱን ሲያዩዋቸው በኢትዮጵያ የአይነ ስውራን ማሕበር በዓል ላይ በመገኘታቸው ደስተኛ የሆኑ ይመስላል። እኔም ሌሎች አዲስ የማክዳ ጓደኞችን ልተዋወቅና ደስ የሚል ቀን ላሳልፍ ስለምችል ደስተኛ ነበርኩ።የጉዟችን መጠናቀቂያ ጊዜ እየተቃረበ ነው። የጎረቤታሞቹ በአል የአዲስ አበባው ጉዞዋችን ማጠቃለያ ይሆናል።.

ሁላችንም ደስ ብሎን ወደ ሚኒባሳችን ገባን። ሚኒባሱን ከሚያሽከረክረው አቢ አጠገብ ብራኢሊ ተቀምጧል። አንድ ላይ ሆነው ከራዲዮ ከሚሰማው ሙዚቃ ጋር አብረው ያዜማሉ። ከኋላ በኩል ድንቂ፣ ካሸንና ኤዲ ተቀምጠዋል። ድንቂ ይዛው የነበረውን ቆሎ በሚስጢር ለሶስቱ አካፈለቻቸው። ማክዳና እኔ በአውቶቡሱ የመጨረሻ ወንበር ላይ ነው የተቀመጥነው። ማክዳ የለበሰችው የሚያምር ጥለት ያለው የባህል ቀሚስ በነጠላ ነው፡ “ይህ ልብስ ስሙ ነጠላ ይባላል” ብላ አስረዳችኝ። በጣም ቆንጆ ሆናለች፤ እንደገና ልንለያይ ስለሆነ ትንሽ እንደማዘን ብያለሁ። በዚህን ወቅት ሚኒባሱ መንገዱ ላይ ያለ ጉድጓድ ውስጥ ገብቶ በሀይል ተንገጫገጨ። ሁላችንም ወደ ላይ ዘለልን። የአደጋ ጊዜ ቀበቷችንን በሆዳችን ዙሪያ ማሰራችን ጠቅሞናል። ከዛም አውቶቡሱ ከተለመደው በላይ ያቃስትና ያጓራ ጀመር። ትንሽ ቆይቶም ሞተሩ ተንተፋተፈ፤ መሪው ጋር ያለው ባለቀለሙ የመኪና ቦርድ ማሳያ ብልጭ ድርግም ብልጭ ድርግም አለ፤ ከዛም ሞተሩ ቀስ በቀስ እየደከመ መጣና በስተመጨረሻም ጠፋ። አቢ በተደጋጋሚ ሞተሩን ለማስነሳት ሞከረ። ሆኖም ግን አልተሳካለትም፡ ፡ሚኒባሱ ቀጥ አለ። “አሁን ምንድን ነው የሚደረገው?” ብሎ በተጨነቀ ሁኔታ ብራኢሊ ጠየቀ። “ቆይ አንድ ጊዜ” ብሎ አቢ አምባረቀ፤ ከዛም በሹፌሩ በኩል ያለውን የሚኒባሱን በር በሐይል ወርውሮ ዘጋውና ወረደ። “’ሂሂሂ! አሁን በእግራችን ልንሄድ ነው” ከዛም ደስ የሚል ዘፈን እየዘፈነ ከመኪናው ጣራ ላይ የታሰረውን ተንቀሳቃሽ ወንበር መፍታት ጀመረ። “ጓደኞቼ ተንቀሳቀሱ፤ ከአውቶቡሱ ውረዱ” ብሎ በተከፈተው መስኮት በኩል ነገረን። የአይነ ስውራኖቹ ማሕበር ሩቅ አይደለም በእግራችን እንደርሳለን አለ። አውቶቡሱን በኋላ እኔው አስብበታለሁ። ታውቃላችህ አይደል? “ ችግር የለም፤ መፍትሔ ብቻ ነው ያለው” ብሎ በአይኖቹ ጠቀሰን። አቢ የሚያጋጣሙ ያልተጠበቁ ነገሮችን እንዴት እንደሚያስተናግዳቸው በጣም ያስገርሙኛል።



ከዛም ከአውቶቡሳችን ወርደን ቀሪውን መንገድ በእግራችን ተያያዝነው። የአዲስ አበባ መንገድ በጣም የጨናነቀና ጩኸት የበዛው ነው። የእግረኛ መሻገሪያና የመንገድ ላይ ትራፊክ መብራት በብዛት የለም። ሁሉም ነገር ድብልቅልቅ ያለ ነው። በከተማው ትላልቅ መንገዶች ላይ ለአይነ ስውራን የሚሆኑ መንገዶች ስላሉ ደስ ብሎኛል፤ ምክኛቱም ብራኢሊ ያለ ችግር መንቀሳቀስ ይችላልና፡
፡ አንድ በጣም መኪና የሚበዛበትን መንገድ ጥግ ይዘን ነው የምንጓዘው። በመንገዱ ግራና ቀኝ ብዙ ሙዝ፣ ሀባብ፣ አፕልና የተለያዩ አታክልቶች የሚሸጡባቸው በተለያየ ቀለም ያሸበረቁ ሱቆች ተደርድረዋል። አነስተኛ ኪዎስኮች ደሞ ቆሎ፣ ውሐና ሎሚ ይሸጣሉ፡
፡ ትንሽ በእግራችን ስለተጓዝን ውሐ ጠምቶን ነበርና ውሀ ለመግዛት ከሱቆቹ መሐል ወደ አንድ አነስተኛ ሱቅ ገባን። እኔና አቢ ውሐ ገዛን፡
፡ ድንቂና ካሸን ደሞ ሎሚና ቢበሉት ቢበሉት አልጠግብ ያሉትን ቆሎ ገዙ። ኤዲ ነጠላ ለመግዛት ፈልጓል፤ ስለሆነም በጀርባው ላይ ካዘለው ቦርሳ ውስጥ ስብርባሪ ገንዘቦች እየፈለገ ነው።



በድንገት “ብራኢሊ ተጠንቀቅ!” ብላ ማክዳ ጮኸች፤ ሆኖም ግን አርፍዳ ነበር። ወዲያውኑ ሀይለኛ የግጭት ድምጽም ተሰማ፤ ብራኢሊም “አዋዋዋዋ” ብሎ ጮኸ፡
፡ “ይሄ አይሆንም፡ ምንድን ነው የተፈጠረው ብዬ በመጨነቅ ጠየቅሁ”። እኔ በተንቀሳቃሽ ወንበር ላይ በመቀመጤ የተነሳ እንደ ቆሙት ሰዎች ሁሉም ነገር በደንብ አይታየኝም። ከዛም የተፈጠረውን ነገር ለማየት ቻልኩ፡
፡ እኛ ሎሚና ወሃ በምንገዛበት ሰዓት ብራኢሊ ቀስ ብሎ የአይነ ስውራን መምሪያ መንገዱን ተከትሎ እየሄደ ነበር። ከሱቁ ትንሽ አለፍ ብሎ ወደ አንድ ግቢ መግቢያ ላይ የአይነ ስውራን መምሪያ መንገድ መስመሩ ላይ አንድ እመኪና ቆሟል፡
፡ ብራኢሊም ማየት ስለማይችል ባለ በሌለ ሓይሉ ከመኪናው ጋር ተጋጨ፤ “አውውው! ብራኢሊ ጉልበቱ ተጎድቷል። ትንሽም ደም እየፈሰሰው ነበር። እኔ በሰዎች ቸልተኝነት በንዴት ጦፌያለሁ። ያለ ምክንያት አይደለም የአይነ ስውራን መንገድ መስመር ከሌላው ተለይቶ የተለየ ቀለም ያለው። ይህ በቀላሉ ሊታይ የሚችል ነው፡
፡ አይናማዎችም ትንሽ ለሌሎች ሰዎች ጥንቃቄ ሊያደርጉ ይገባል። እኛ ጋር፤ ሳይፐዚግም የአይነ ስውራን መንገድ ላይ መኪናና ብስክሌት እያቆሙ መንገዱን በመዝጋት ለአይነ ስውራን አደጋ ይሆናሉ። ማክዳ ባጣም እንደተናደድኩ አየችና፡- “አህ ሌዎን፤ አትናደድ። ብዙ ጊዜ የአይነ ስውራን መስመርን ሰዎች ልብ ሳይሉት ነው የሚዘጉት” አለች። በዚህ ሰዓት የመኪናው ባለቤት ደረሰ፡
፡ እንደደረሰም የተፈጠረውን አይቶ በተደጋጋሚ ይቅርታ ጠየቀ፡
፡ አሁን ማክዳ ያለችው ገባኝ። ብራኢሊን ለመጉዳት ብሎ ያደረገው ነገር አልነበረም፤ ጥንቃቄ ባለማድረጉ የተነሳ አዝኗል፡፤ ብራኢሊና ሹፌሩ በእጃቸው ተጨባበጡ፤ ቀጥሎም ተቃቀፋ። ብራኢሊ ደስ የሚል ባለ ቀለም ፕላስተር የቆሰለው ጉልበቱ ላይ ተደረገለት።



እኛ ከሹፌሩ ጋር ስንከራከር ኤዲ፣ ድንቂና ካሸን ከሱቆቹ አጠገብ የሚገኝ አግዳሚ ወንበር ላይ ቁጭ ብለው ይጠብቁን ነበር፡፡ ካሸን የሆነ ጥግ ላይ አንድ አዲስ ነገር እስኪያይ ድረስ፤ ሎሚያቸውን እየጠጡ ቆሎዋቸን ይቆረጥሙ ነበር፡፡ ቀስ ብሎ ተጠጋትና የሚያበራውን ቀዩን አይኗን አየው፡፡ “ይሄ እኮ የአስቴር አይን ነው” ብሎም አሰበ፡፡ ከዛም ከጅቧ ጋር የነበረውን ግራ አጋቢ የነበረ የተገናኙበትን አጋጣሚ አስታውሶ በጀርባው በኩል ቀዝቃዛ ላብ ሲወርድ ተሰማው፡፡ ከዛ በፍጥነት ዞሮ ጓደኞቹ ወዳሉበት አቅጣጫ ተፈተለከ፡፡ ተከትላው ይሆን? ምንድን ነው የምትፈልገው? ሆዱ ሲረበሸበት ተሰማው፡፡ አቢ ጮክ ብሎ “ጓደኞቼ” ብሎ ተጣራ፡ ፡ የእረፍት ሰአታችን አልቋል፡፡ መንገዳችንን እንቀጥል፡፡
ካሸን ጓደኞቹ በመንቀሳቀሳቸው ተደስቷል፡፡ ከዚህ ከሚያስፈራ እምባ ያቀረዘዘ ባለ ቀይ አይን ከሚገኝበት አካባቢ መጥፋት ነው፡፡



# የተከፋው አውሬ

አቢ ደስተኛ ሆኖ በጥርሶቹ መሐል ያፏጫል፡፡ የላይኛው የሰውነቱ አካል ከሙዚቃው ምት ጋር አብሮ ይውረገረጋል፡፡ ሰው እንደዚህ ከላይ እስከ ታች ሲናጥ ማየት ያስቃል፡፡ በእግራችን ጥቂት ከተጓዝን በኋላ የአይነ ስውራን ማሕበር ጋር ደረስን፡፡ ወደ አንድ ትልቅ ግቢ የሚያደርሰው የመግቢያ በሩ የተለያዩ ቀላማት ባለቸው አበቦችና ጨርቃ ጨርቅ አጊጧል፡፤ በአይነ ስውራን ማሕበሩ ቅጥር ግቢ ውስጥ ከአንድ ትልቅ መድረክ ፊት ለፊት ቆመናል፡፡ ከኋላችን በርካታ የተለያየ ነገር መሸጫ ቦታዎች አሉ፡፡ በጣም ደስ የሚል የቆሎ ሽታ ያውዳል፡፡ ከአጠገባችን በባሕላዊ መንገድ የተፈላ ቡና ሚሸጥበት መሸጫ ቦታ አለ፡፡ ቡና ተብሎ ነው የሚጠራው፡፡ ባለ ቀለም በሆነ አነስተኛ ስኒ ነው የሚቀርበው፡፡ የቡናው ስነስርዓት ሲካሄድ መሬቱ ላይ ሳር ይነሰነሳል፡፡ ቡናው በአንድ ብረት ምጣድ ላይ ይቆላል፡፡ በስተመጨረሻም የተፈላው ቡና ረጅም አንገት ባለው ጀበና በየስኒው ላይ ይቀዳል፤ አብሮም ፈንድሻ ይቀርባል እያለች ማከዳ እያስረዳችን በአንድ ትልቅ ማንኪያ ቡናው ውስጥ ስኳር ጨምራ ታማስል ገባች፡፡ “ፈንድሻውን ብቻ መብላት ይቻላል?” ብሎ ኤዲ ጠየቀ፡፡ “ቡና ብዙም አልወድም” አለ ከዛም በሁለት እጆቹ ፈንድሻውን አፈሰና ከድንቂ ጋር አብረው ይበሉ ጀመር፡፡



መድረኩ ላይ አንድ ኦርጋንና አንድ ከበሮ ተዘጋጅቷል። አራት ሙዚቀኞች ወደ መድረኩ ላይ ወጡ። ሁሉም አይነ ስውራን ናቸው: : ሁሉም ዥንጉርጉር ሸሚዝ ያደረጉ ሲሆን ትንሽዬ ቢራቢሮ ክራቫትም አንገታቸው ላይ አስረዋል። ከኦርጋኑና ከከበሮው አጠገብም በኤሌክትሪክ የሚሰራ ጊታርና ባዝ አለ። ሙዚቀኞቹ መሳሪያዎቻቸውን አነሱ፤ ከነሱ ውስጥ አንዱ ድምጽ ማጉያውን አንስቶ የተወሰኑ ቃላቶች በአማርኛ ተናገረ። ማክዳ ለኛ ታስተረጉምልናለች: : “አይነስውራን አሳዎች” የተሰኘ የብሔራዊ አይነ ስውራን ማሕበሩ (ኢ ኤን አ ቤ) በመባል የሚጠራው የሙዚቃ ቡድን ነን ነው ያለው አለች። ብራኢሊ ሳቀ። በሳምንት ሁለት ቀን፤ እዚህ በማሕበሩ ቅጥር ግቢ ውስጥ ነው የሚለማመዱት። ሁሉም ሙሉ በሙሉ አይነ ስውራን ናቸው፤ ሆኖም ግን ይሄ ልባቸው የሚያዛቸውን ለማድረግና ሙዚቃ ለመጫወት አያግዳቸውም”። ገባኝ። ዋናው ነገር ሙዚቃው ነው፤ ሌላው ዋጋ የለውም። ከዛም ጥቂት ቆይቶ ሙዚቃው ተጀመረ። በጣም ነው የተደነቅሁት። ብራኢሊ ተደስቶ አብሮ ያጨበጭባል፤ ከፊተኛው ረድፍ ላይ ኤዲና ድንቂ ይደንሳሉ።







ሰው ሁሉ
እየተዝናና ”የአይነ ስውራን አሳዎችን”
ሙዚቃ ሲያጣጥም ትንሹ ካሸን በተንቀሳቃሽ ወንበሩ ወደ መጸዳጃ ቤት ሄደ። መጸዳጃ ቤቱ የሚገኘው ከዋናው ሕንጻ በስተጀርባ በኩል አንድ አነስተኛ ቤት ውስጥ ነው። ጥጉ ላይ ሲደርስ ታጥፎ በትልልቆቹ ዛፎች ቅርጫፍ የተነሳ ጨለም ወዳለ በእንጨት ወደታጠረ ቤት አመራ። እየራቀ በሄደ ቁጥር የሙዚቃው ድምጽ እየቀነሰ ሄዶ በድንገት ወደ መጸዳጃ ቤቱ የሚወስደው ቀጭን መንገድ ላይ ብቻውን ቀረ። ከዛ በድንገት የሚንኳኳ ነገርና የሚያንኮራፋ ድምጽ ሰማ። ከአንዱ ዛፍ ጀርባ አንድ ጥቁር ጥላ ወጣና ከኋላው ይዞ

ወደ ግራና ቀኝ ያወዛውዘው ጀመር። ካሸን መጫወቻ ቦታው ላይ የተዋወቃትን የአስቴር ጅቧን የሚያበሩ ቀያይ አይኖች አየ፡
፡ “ካሸን፤ አሁን እዚህ ብቻህን ነው ያለህው” እያለች ዙሪያውን ትዞረው ጀመር። “አይደለም፤ አለ ካሸን በሚንቀጠቀጥ ድምጽ” “እኔ እዚህ ያለሁት ከጓደኞቼ ጋር ነው” “ያንተ ጓደኞች፤ አሓ፡
፡ እንደሚመስለኝ እነሱ በሙዚቃው ተጠምደዋል። ስለሆነም አንተ እዚህ ያለኸው ብቻህን ነው። ከኔ ጋር! አሃሃሃሃርርርርርር”።የአስቴር ግራ የሚያጋባ ሳቅ ካሸንን ከላይ እስከታች ወረረው። ልቡ በሐይል ትዘላለች፤ ከሚገባው በላይ ፈርቷል። አፏ እየሰፋ እየሰፋ ይሄዳል፡
፡ ካሸን ከመፍራቱ የተነሳ ልቡ በአንገቱ ልትወጣ እየታገለው ነው። ከመፍራቱ የተነሳና ትበላኛለች ብሎ ስላሰበ ፊቱን በእጆቹ ሸፈናቸው።



“(
ሊሆን አይችልም” አለ የሆነ ሰው ከምታስፈራው ጅብ በስተጀርባ በኩል። ካሸን አይኖቹን ከፈታቸው፤ ኤዲና ድንቂ!
ድንቂ፤ አስቴርን በያዘችው ምርኩዝ አፍንጫዋን ስትመታት ኤዲ ደሞ ጭራዋን ይዞ በሐይል ጎተታት። “ጓደኞችንን ተይው!” አለ በጣም ተቆጥቶ ኤዲ። ጅቧም መሬት ላይ ቁጭ አለች። “አዋዋ” አለች ድምጿን ዝቅ አድርጋና አፏ እዳዋን እያሻሸች። “አፍንጫዬ በሽተኛ ነው!” አለች፡
፡ እንዲህ ከሆነ ታዲያ ጓደኞችን ካሸንን መተናኮል አልነበረብሽም፡
፡ አስጠሊታ አውሬ አለቻት ድንቂ በመጠየፍ አይነት እያየቻት።



አስቴር ግራ ተጋብታና አዝና የሶስቱን ጓደኞሞች ፊት ታያለች፡
፡ አይኖቿ በእንባ ተሞሉ፤ ከዛም ቀስ ብሎ እንባዋ ይፈስ ጀመር፡፤
“አዝናለሁ” የሚል ቃል ፈንቅሏት ወጣ። ለምንድን ነው ግን ተንቀሳቃሽ ወንበሩን መንጠቅ የፈለግሽው? አንቺ እንደሆነ ተንቀሳቃሽ ወንበር አያስፈልግሽም። ብሎ ኤዲ በመገረም ጠየቃት። “ታሪኩ በጣም ረጅም ነው” ብላ አስቴር በእንባ ታጅባ ትተርክላቸው ጀመር። “ለሰው አይታይም እንጂ በአንድ ወቅት አደጋ ደርሶብኝ አንድ አይኔ ፈጽሞ ማየት አይችልም። ስለሆነም ለአደን ስንሄድ ከቡድናችን ሁሉ ጥሩ የማልሆነው እኔ ነበርኩ። እንዲያውም ለአደን መሄድ ራሱ አልፈልግም ነበር፡
፡ በጣም ነው የምጠላው። እንጀራ በሚጣፍጥ ወጥ ብበላ ይሻለኛል፡
፡ ሆኖም ግን እኛ ጋር ጥብቅ የሆነ መመሪያ ነው ያለው። መመሪያውን ያላከበረ ደሞ ከቡድኑ ይባረራል። በዚህም የተነሳ ከብዙ ወራቶች ጀምሮ ከቤተሰቦቼ ተለይቼ ብቻዬን መንገድ ላይ ነው የምኖረው።



በዚህ ጊዜ ኤዲ፣ ድንቂና ካሸንም አዘኑ። ከዚያም በመቀጠል “ታዲያ ሴት አያቴ በጣም ስላረጀችና በዚህም የተነሳ በእግሯ መራመድ ስለማትችል ይህንን ተንቀሳቃሽ ወንበር ብወስድላት ብዬ አስቤ ነው። ምናልባትም ተደስታ ወደ ቡድኑ መልሳ ታስገባኝ ይሆናል በሚል ነው”። አስቴር ማልቀሷን ቀጠለች። ሁላችንም ምን መናገር እንዳለብን አልገባንም። አስቴር በካሸን ላይ ያደረገችው ትክክል አይደለም። ሆኖም ግን ደሞ ታሳዝናለች።





“እርስ በእርሳችን መረዳዳት፤ አንድ ላይ ወይም በሕብረት መኖር” አልኩ። ሌዎን! ብሎ ኤዲ ተጣራ። እናንተ የት እንዳላችሁ ጠፍጣችሁብኝ የት ሄዱ እያልኩ ስፈልጋችሁ ነበር” ብዬ መለስኩ። “አስቴር ያደረገችውን ሰምቻለሁ። እንደሚመስለኝ ልንረዳት የሚገባን ይመስለኛል። ብቻዋን ናት፤ እንዴት አድርጋ ራሷን መርዳት እንዳለባት አታውቅም”። “ትክክል ነው” አለ ኤዲ። “ብቻ መሆን በጣም መጥፎ ነው፤ ከፈለግሽ ከኛ ጋር መሆን ትችያለሽ” አላት። አስቴር በመደነቅ አየችን፡፤ ሁላችንም በአዎንታ አንገታችንን አወዛወዝን። ፊቷ ባንድ ጊዜ በሳቅ ተሞላ። “አስቀያሚ አውሬ ስላልኩሽ ይቅርታ አድርጊልኝ” አለች ድንቂ። “አንቺ ምንም አስቀያሚ አይደለሽም፤ ተንቀሳቃሽ ወንበር የማትሰርቂ ከሆነ ደሞ አውሬም አይደለሽም”። አስቴር ሳቀች። ሁላችንም ወደ መድረኩና ወደ ሌሎቹ ጓደኞቻችን ሄድን፡ ፡ አስቴር ለመጀመሪያ ጊዜ እንጀራ  አገኘች። ከእህል ብቻ የተሰራ።



# ሁለት ልቦችና አንድ አዲስ ሐገር

ከእንቅልፍ መቀስቀሻ ሰአቱ ሲጮህ የጸሐይዋ ብርሓን የፊቴን ጺም እየለበለበው ነበር። ወቅቱ የጸደይ ወቅት ነው፤ የአእዋፋቶቹ ጬኽት ያስደስተኛል፤ ደስ የሚል የመጋቢት ወር መጀመሪያ ነው፡ ፡ አስደሳች ከነበረው የኢትዮጵያ ጉዞዬ ከተመልሰኩ ብዙም አልቆየም፡ ፡ ወደ መኖሪያ ከተማዬ ላይፕዚግ ተመልሻለሁ። እንደ ስሟ አዲስ የሆነችው አዲስ አበባ በርካታ ደስ የሚሉና የማይረሱ ትውስታዎችን ትታልን አልፋለች። በተለይ ደሞ ከአዎሮፓ በብዙ ርቀት ላይ አዳዲስ ጓደኞች ለማፍራት በመቻሌ በጣም ደስተኛ ነኝ። እናም አዲስ አበባም እንደ መኖሪያ ከተማዬ አይነት ስሜት እንዲኖረኝ የሚያደርግ ስሜት ይዞኛል። በደረቴ ውስጥ ሁለት ልቦች ናቸው ምት የሚመቱት፤ አንዱ ለላይፕዚግ ሌላኛው ለአዲስ አበባ። 64 በድንገት ሌላኛው ክፍል ውስጥ ጲጲጵ የሚል ድምጽ ተሰማ። ምን ሊሆን እንደሚችል እርግጠኛ ነበርኩ። ኢሜይል መጥቶልኝ ነው፡ ፡ ፈጠን ብዬ ወደ ኮምፒዩተሬ ሄድኩ። ማክዳ እንደምትጽፍልኝ ቃል ገብታልኝ ነበር፤ በእርግጥም ኢሜይሉ የሷ ነበር።

**ውድ ሌዎን፤**

**ደህና እንደሆንክ ተስፋ አደርጋለሁ።ወደ ላይፕዚግ በሰላም በመድረሳችሁ በጣም ደስ ብሎኛል። ሌሎቹስ እንዴት ናቸው? ሌሎቹ የኢትዮጵያ ጓደኞቻችን ሰላምታ አቅርበውላችኋል። ካሸን በትጋት ለትምሕርቱ በመዘጋጀት ላይ ይገኛል፡ ፡ ላንተ የመንቀሳቀሻ ወንበር ምስጋና ይግባውና በየቀኑ ከትምሕርት ቤቱ ፊት ለፊት ከጓደኞቹ ጋር ይገናኛል። አቢም ሚኒባሱን በጥሩ ሁኔታ አሳድሶታል። አሁንም በአዲስ አበባ መንገዶች ላይ ከታች ወደ ላይ እያለ ሲጮህ ይውላል። የእሱ ዘፈን ይሁን መኪናው በሀይል የሚጮሁት ማንም የሚያውቅ የለም። ድንቂ ወደ ሙዚየሟ ተመልሳለች፡፤ እዛ ያሉት ከሷ ጋር ለዘመናት አብረዋት የኖሩት ናፍቀዋት ነበር። እኛም በፈለግን ጊዜ እየሄድን ልንጎበኛት እንችላለን። አስቴርና እኔ በጣም ነው የምንግባባው። ስለዚህም እኔ ጋር ነው የምትኖረው፡ ፡ አንድ ላይ ሆነን እንጀራ እንጋግራለን፤ ልብስ መጥለፍም አስተምሬታለሁ። አንድ ላይ ሆነን እንደሰታለን። እውነትህን ነው፤ "አንድ ላይ ወይም በጋራ" የሚለውቃል መሪ ቃል ነው። ይህንን ልናከብር ይገባናል። ምናልባትም ላይፕዚግ እንገናኝ ይሆናል። ስለዚህ ጉዳይ በጋራ እናስብበት!**
**ያንተው ማክዳ**

ቆሎዬን እየቆረጠምኩ፤ እሺ እሺ እያልኩ ማሰብ ጀመርኩ!



# ትርጓሜ

**አምስት ኪሎ** አዲስ አበባ ውስጥ የሚገኝ የአንድ አካባቢ ስያሜ ነው።

**ቡና** የኢትዮጵያ ቡና ስያሜ ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ ቡና በብዛት በባሕላዊ መንገድ ነው የሚፈላው። በመጀመሪያ አረንጓዴው የቡና ፍሬ ይታጠብና በከሰል ላይ ይቆላል። ከተቆላ በኋላ የጠቆረው ቡና በቡና መውቀጫ ይወቀጥና ወደ ቡና ማፍያው (ጀበና) ውስጥ ይጨመራል ውኃም ይደረግበታል። የጀበናው ውኃ እስከሚፈላና እንፋሎት እስከሚያወጣ ድረስ እሳቱ ላይ ይጣዳል። ቡናው ለመጠጣት መራር ስለሚሆን በርካታ ማንኪያ ስኳር ለማጣፋጫነት ይጨመርበታል። ብዙ ጊዜ ከቡና ጋር ፖፕኮርን አብሮ ይዘጋጃል።

**እንጦጦ** ከአዲስ አበባ በስተሰሜን ምስራቅ አቅጣጫ የሚገኝ የተራራ ሰንሰለት ጫፍ ነው። ከፍታውም 3200 ሜትር ሲሆን በባሕርዛፍ ደን የተሸፈነ ነው። ተራራው እንደ ቅዱስ አካባቢ የሚታይ ሲሆን በውስጡም በርካታ ገዳማትና ቤተክርስትያኖች እንዲሁም የምኒሊክ ሁለተኛና የባለቤታቸው እቴጌ ጣይቱ የቀድሞ ቤተ መንግስትም ይገኝበታል።

**ሐይለሥላሴ አንደኛ** (በ 17 ሀምሌ 1884 ሐረር አቅራቢያ ተወልደው በ 21 ነሐሴ1967 አዲስ አበባ ውስጥ አረፉ) ከንግስና በፊት የነበራቸው መጠሪያ ስማቸው ተፈሪ መኮንን የሚል የነበረ ሲሆን የአቢሲኒያ የመጨረሻው ንጉስም ናቸው። ይሕም በምስራቅ አፍሪካ የአሁኖቹ ኢትዮጵያና ኤርትራ ውስጥ የነበረ የንጉሳዊ አገዛዝ ነበር። ሐይለሥላሴ እራሳቸውን 225ኛው የንጉስ ሰለሞን ወራሽ ነኝ ብለው ሰይመው ነበር። በራስ ተፈሪዎች እምነት ሐይለሥላሴ ወደ ምድር የተላኩ መሲሕ ተደርገው ይከበራሉ።



**እንጀራ** ኢትዮጵያ ውስጥ በባሕላዊነት የሚበላ ሥሥ ዝርግ ዳቦ ነው: : የሚሰራውም የጤፍ ዱቄትን በውሐ በማቡካት ከሚገኝ ሊጥ ነው: : የሚበላው በቀኝ ዕጅ ሲሆን ዕንጀራ እንደ ምግብ መመገቢያ (ሹካ ማንኪያ) ጭምርም ያገለግላል። በአንድ ትልቅ ትሪ ላይ ዕንጀራ ተደርጎ ስጋ፣ አትክልት እንዲሁም ፓስታና የተለያዩ የወጥ አይነቶች በላዩ ላይ ተደርጎበት ይቀርባል። ከዛም በጋራ አንድ ላይ በመሆን ከእንጀራው ላይ በትንሽ በትንሹ እየቆረጡና ከስጋውና አትክልቱ እያጣቀሱ ይበላል።

**እሺ እሺ** ወይም “እሺ” በጣም ጠቃሚ የሆነ የአማርኛ ቃል ሲሆን ትርጉሙም “አኬ” “አዎ” “ጥሩ” “ተስማምቻለሁ” እንደማለት ነው።

**ቆሎ** ከገብስ የሚዘጋጅ የኢትዮጵያ ባሕላዊ መክሰስ (ምግብ) ሲሆን ብዙ ጊዜ ከቡና ጋር አብሮ ይቀርባል። በተጨማሪም ከቁርስ ምሳና ዕራት ውጪ በየመሐሉ ይበላል። ጥራጥሬው በጥንቃቄ በእሳት ሲቆላ ጣፋጭ ጣእሙ ከውስጡ ስለሚወጣ ድንቅ ጣዕም ይኖረዋል።

**ሉሲ** በጣም ጥንታዊ የሆነ ከሞላ ጎደል ሙሉ ለሙሉ ሊባል በሚቻል መልኩ የተገኘ የሰው ልጅ ቅሪተ አካል ነው።ከ 3 ሚሊዮን ዓመት በላይ ዕድሜ እንዳለው የሚገመተው ቅሪተ አካል በአሁኑ ሰዓት የሚሊዮኖች መኖሪያ ከተማ በሆነችው አዲስ አበባ ውስጥ ብሔራዊ ሙዚየም ውስጥ ለዕይታ ቀርቧል። የሉሲ አጽም በ 1966 ዓ.ም. ኢትዮጵያ ውስጥ ሐዳር የሚባል አካባቢ በተደረገ ቁፋሮ ነው የተገኘው: : ተመራማሪዎቹ የቢትልስን “ሉሲ በሰማይ ከዳይመንድ ጋር” (ሉሲ ኢን ዘ ስካይ ዊዝ ዳይመንድስ) የሚለውን ዘፈን ሲሰሙ ግኝቱን በማስተዋወቃቸው በጣም ደስተኞች ናቸው። ብዙዎች ቅሪተ አካሉን ድንቅነሽ እያሉ ይጠሩታል። በአማርኛ “ታምሪያለሽ” እንደማለት ነው።

**ንጉስ ሚኒልክ ሁለተኛ** (በ 12 ነሐሴ 1836 አንኮበር ተወልደው በ 03 ታሕሳስ 1906 አዲስ አበባ ውስጥ አረፉ) ከ 1881 እስከ 1906 ድረስ የኢትዮጵያ ንጉስ ነበሩ: : ከባለቤታቸው እቴጌ ጣይቱ ጋር ከእንጦጦ ተራራ ስር አዲስ አበባን የቆረቆሩትም እሳቸው ናቸው።

**ሰላም** በአማርኛ “ሐሎ” ለማለት የሚያገለግል ቃል ነው፡፡

**በከተማ ውስጥ ያለ ከተማ** የአካል ጉዳተኛ የሆኑ ሰዎችም ሊሳተፉበት የሚችል ላይፕዚግ ውስጥ በሚገኝ ሀውስ ሽታይን ሽትራሴ በሚሰኝ ማሕበር መሪነት የተዘጋጀ የእረፍት ጊዜ ጫወታ ሲሆን ታዳጊዎችና አዋቂዎች የሚጫወቱት የጫወታ አይነት ነው፡ ፡ ጨዋታውን የሚጫወቱት ሰዎች በፈለጉትና በሚያስቡት መልኩ የፈለጉትን ከተማ ይገነባሉ፡፡ ይሕ የጫወታ አይነት ኢትዮጵያ ውስጥ ካሉት የፕሮጀክቱ ተስታፊዎች ጋር በጋራ በመሆን የበለጠ ተሻሽሎ ወደ አዲስ አበባም እንዲሄድ ተደርጓል፡፡
በጉዳዩ ላይ ተጨማሪ ማብራሪያ ከፈለጉ:
- www.haus-steinstrasse.de/projekt/stadt-in-der-stadt/

**ወጥ** አንድ የኢትዮጵያ የምግብ አይነት ስያሜ ሲሆን የተለያየ የወጥ አይነትም አለ፡፡ በተለምዶ የሚበላውም በዕንጀራ ነው፡፡ ወጥ ከአትክልት እንዲሁም ከከብት ስጋ ወይም ከዶሮ ሊሰራ ይችላል፡፡



# የብሬል ፊደሎች





ዋናው መነሻ
(በ 6 ነጥቦች የሚጻፍ ነው)



የቁጥር ምልክቶች
(ከእያንዳንዱ ቁጥር ፊት
መጻፍ ይኖርበታል)





# የጣት ምልክቶች





# ስዕሎች (ፒክቶግራም)



የሕንጻ መግቢያ ለአካል ጉዳተኛ



በቂ የአካል ጉዳተኛ መግቢያ
የሌለባቸው ሕንጻዎች




የመኪና ማቆሚያ ለአካል ጉዳተኛ



አንሳሰር ለአካል ጉዳተኛ



አሳንሰር ለአካል ጉዳተኛ በበቂ ሁኔታ የለውም




ለአካል ጉዳተኛ መጸዳጃ አለ



ለአካል ጉዳተኛ መጸዳጃ በበቂ ሁኔታ የለም



ልዩ እና በግል ሊሰጡ የሚችሉ
የዕርዳታ አገልግሎቶች



መስማት ለተሳናቸው የሚሰጥ ዕርዳታ



በደንብ ለማያዩና ለዓይነ
ስውራን የሚሰጥ ዕርዳታ

# የሎርም ፊደላት






# “በጫወታ አካታችነትን መማር”

**የአካታችነት የመማሪያ ቦርሳ ፕሮጀክት በላይፐዚግ የጋራ ማሕበር (ዳስ ለርንኮፈርፕሮየክት ደስ ቤሂንደርተንፈርባንደስ ላይፐዚግ ኤ.ፋው)**




የአካታችነት የመማሪያ ቦርሳ ፕሮጀክት የተዘጋጀው በላይፐዚግ የጋራ ማሕበር ነው። በውስጡም መጽሐፍቶች፣ እያዳመጡ የሚጫወቱባቸው ዕቃዎች፣ አሻንጉሊቶች፣ የተለያዩ ጨዋታዎች እና እነዚህን ለመሞከሪያ የሚሆኑ ዕቃዎች አሉት። እነዚህ ዕቃዎች የመጀመሪያ ደረጃና ቅድመ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ያሉ ታዳጊዎችን በጫወታ መልክ ስለአካታችነት እውቀት እንዲጨብጡ የሚያስችሏቸው ናቸው። በሳክሶኒያ ውስጥ 50 የተለያዩ ቦታዎች የመማሪያ ቦርሳዎቹን መዋስ ይቻላል።

**ተጨማሪ መረጃ ከዚህ በሚከተለው ድሕረ ገጽ ያገኛሉ፡-**
**www.behindertenverband-leipzig.de**

# ምስጋና

ለአዲስ አበባ ቲቪኢቲ ቢሮ እና ኢንጌ ቦዘንሀርድት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲና ዶር. ሰዋለም ጸጋ፣ በላይፕዚግ የጀርመን አካታች የንባብ ማዕከል (ዲዜድቢ ንባብ) እና ወ/ሪት (ወ/ሮ) ካሮሊን ሹረር፣ ዩሊያኔ አይልሃርድት የዲዜድ ንባብ ማዕከል ድጋፍ ማሕበር እና ሉድቪግ ሄኔ፣ ጌኔራትሲዮንስሆፍ ጌጌኤምቤሐ፣ የጀርመን ቤተክርስትያን ት/ቤት እና መርዳሳ ካሳዬ፣ ሐውስ ሽታይን ሽትራሴ ማሕበር እና ኡልሪኬ ቤርናርድ፣ ፖሊ ቻርሎቴ ሆህሌ፣ የላይፕዚግ የሞዴሎች ትምሕርት ቤት፣ ሌጎ ብራኢሌ ብሪክስ (LEGO®-Braille Bricks), ካሪን ናቡኢኬ፣ ኤንጂአ ቱጌዘር! እና ሐብታሙ ሻውል፣ ሚሪያም ፕፌፈር፣ ማርኩስ ፕሱሬክ፣ የላይፕዚግ ከተማ / የአለማቀፍ ግንኙነት ክፍል እና ካትያ ሮሎፍ፣ የቶማስ ቤተሰብ፣ ፍራንሲስካ ቫልተር፣ አንድሬ ቪንክለር እና ዮርግ ቪንክለር።

